# ካርቦን-ኮፒ ክርስትና



## ዶክተር መለሰ ወጉ

## በዶ/ር መለሰ ወጉ ተጽፈው የቀረቡ ሌሎች መጻሕፍት

- ስሜት ያለቦታው
- በጸሎት፥ የማይቻለው ይቻላል
- የአዕምሮ ጭንቀት
- ባንስማማ፥ ላለመስማማት እንስማማ
- የመፈስ ቅዱስ ፍሬዎች
- ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ማድረግ
- ጋብቻ፥ እስከ ሞት ወይስ እስከ መፋታት?
- የመንፈ ሰ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም
- እስቲ ምላስህ!
- የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ - ክፍል አንድ
- የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና የመሪዎቿ መሠረታዊ የአመራር ስልት - ክፍል ሁለት
- ከአስቸጋሪ ሰው ጋር አብሮ መኖር! መኀበራበት! መሥራት፣ማምለክ ይቻላል?
- ኢሥርቱ ትእዛዛትና የዘመኑ የሞራል ውድቀት
- እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?
- መንፈሳዊ ውጊያ
- ስንኮከስ እንዳንጠፋፋ
- መስቀል-አልባ ክርስትና

*ካርቦን-ኮፒ ክርስትና*
*"Carbon Copy Kiristina"*
*Carbon-Copy Christianity*

የመጀመሪያ እትም፤ ሐምሌ 2005 ዓ.ም.
First Edition, August 2013

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች፥ እንዲሁም በኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ከታተመው 'አዲሱ መደበኛ' መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ፥ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለማባዛት፥ በቅድሚያ ከኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ዋና ጽሕፈት ቤት የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright © 2013 by Ethiopian Outreach Ministry
All rights reserved. No part of this book may be reproduced in any manner without written permission from Ethiopian Outreach Ministry except in the case of brief quotations in critical articles and reviews.

Produced by:

Ethiopian Outreach Ministry
P.O. Box 2241
York, PA 17405
United States of America

**Ethiopia Office Address:**
P.O. Box 7888
Addis Ababa, Ethiopia
Phone: 011-251-1-156-4268

http://www.eomusa.org

Printed in Ethiopia

## ማ ው ጫ

መግቢያ

ምዕራፍ 1

ሁላችንም አንድ ዓይነት ሆነን አልተፈጠርንም 15

ምዕራፍ 2

ካርቦን-ኮፒ መሆናችን፥ ራሳችንን መጥላታችን ይሆን? 45

ምዕራፍ 3

ካርቦን-ኮፒ ከመሆን፣ ራስን መሆን ይቀላል 77

ምዕራፍ 4

ራስን ማወቅ፣ ካርቦን-ኮፒ ከመሆን ያድናል 109

ምዕራፍ 5

ያልሆኑትን ለመሆን መሞከር፣ ሕሊናን ያስጨንቃል 139

ምዕራፍ 6

ራስን ከሌላው ጋር ማወዳደር አይጠቅምም 165

ምዕራፍ 7

*እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን እንሆን* **191**

ምዕራፍ 8

*ሌላውን ከመምሰል፣ ኢየሱስን እንምሰል* **223**

ምዕራፍ 9

*ያልሆኑትን መሰሎ ከእግዚአብሔር መደበቅ አያዋጣም* **259**

*መደምደሚያ* **295**

*ዋቢ ጽሁፎች* **299**

# መግቢያ

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው መልካም አድርጎ ለራሱ ዓላማ እንዲውል ከፈጠረው፣ ሰው ራሱን መቀበል የሚያቅተው ለምን ይሆን? የክርስትና እምነት በእውነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ አማኝ ለእግዚአ ብሔር፣ ለሰውና እንዲሁም ለራሱ *"እውነተኛ"* የማይሆነው፣ ማንነቱ ለውጦ ያልሆነውን ለመሆን ወይም ለመምሰል የሚሞክረው ለምን ይሆን? ይህን መጽሐፍ አዘጋጅተን ለክርስቲያን አንባቢዎች ለማቅረብ የተነሳ ንበት አንደኛው ምክን ት፣ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሌላው ሰው ግልባጭ ሳይሆኑ፣ *"ራሳቸውን ሆነው"* ማደግ የሚችሉበትን አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦችን ለማካፈል ነው።

እግዚአብሔር *"እኛን፣* ወይም *"ራሳችንን* እንጂ፣ የሌላው ሰው *ካርቦን-ኮፒ* አድርጎ አልፈጠረንም። እኔና እናንተ በምድር ላይ የተወሰ ነልንን ዘመን ጨርሰን ወደ ሰማያዊው ቤታችን ስንሄድ፣ በኃያሉ እግዚአ ብሔር ፊት ስንቀርብ፣ እግዚአብሔር *"ሙሴን፣ ዳዊትን፣ ኤልያስን፣ አስቴርን ለምን አልሆናችሁም?"* ወይም *"ለምን እነሱን አላከላችሁም?"* ብሎ አይጠይቀንም። የሚጠይቀን *"የተፈጠራችሁበትን ዓላማ ለመፈጸም ለምን ራሳችሁን ሆናችሁ አልተገኛችሁም?"* ብሎ ነው። *ጆን ኦርትበርግ (John Ortberg) በሕይወትህ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነው ነገር፣ የምታደርገው ነገር ሳይሆን፣ የሆንከው ወይም ሆነህ የተገኘኸው ነው"* አለ። ስተረጉም አበላሽቼው እንደሆነ በማለት፣ እንግሊዘኛውንም ጭምር አስፍሬአለሁ። *(The most important task of your life is not what you do, but who you become.)*[1] *ይላል።*

ሰው ሌላውን መስሎ ሳይሆን ራሱን ሆኖ ሲያድግ፣ ለብዙዎች በረከት ይሆናል። ራሱን እንዳለ ተቀብሎ ሲኖር፣ ያልሆነውን እንደሆነ አስመስሎ መኖሩን እየተወ ይመጣል። ራሱን ሆኖ መኖርን የሚፈራ ሰው፣ በራሱ እምነት የሌለው ይሆናል። ራሱን መቀበል ካቃተው፣ ሌሎች ሊቀበሉት አይችሉም። እኔና እናንተ መሆን የምንችለውን እንድንሆን

---

[1] John Ortberg. The Me I Want to be, Zondervan, Grand Rapids, MI. 2000.

የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ፈቃዱን የምንፈጽምበት፣ ዓላማውንም ተግባራዊ ማድረግ የምንችልበትን ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ስጦታ ለያንዳንዳችን ሰጥቶናል። በውጪም ሆነ በውስጥ ሌላውን ሳይሆን ራሳችንን ሆነን ስናድግ፣ ለብዙዎች በረከት እንሆናለን።

ወደ ክርስትና እምነት በቅርቡ የመጣውም ሆነ ብዙ ዘመን የቆየውም አማኝ፣ የማያቋርጥ መንፈሳዊ ዕድገት ማሳየት አለበት። መንፈሳዊ ዕድገት እንደ ሥጋዊ ዕድገት ማቆሚያ የለውም። ከጌታው ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ያለው፣ በአገልግሎት ውስጥ ብዙ ዘመን ያሳለፈው ሐዋርያው ጳውሎስም፣ ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ገና ያልሆነ፣ ወይም እድገት ያላበቃ፣ መድረስ ካለበት ደረጃ ገና ያልደረሰ መሆኑን ራሱ ይናገራል፦

- *"አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፤ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ወንድሞች ሆይ! እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቆጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ" (ፊልጵ. 3፥ 12-13)።*

እንግዲህ ወደ ፍጹም ሙሉነት ለመድረስ፣ እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን ለመሆን፣ በእውነት ላይ ተመስርተን፣ ሌላውን ሳይሆን ራሳችንን ሆነን ማደግ አለብን። ዕድገታችንም በሂደት እንጂ በአንድ ጊዜ እንዳልሆነ እናውቃለን። ዛሬ እንደትላንትናው አይደለንም። ነገ ደግሞ እንደ ዛሬው አንሆንም። ይሄም ዕድገታችን በሂደት ላይ እንደሆነ ያሳየናል። በጥሩ ሁኔታ ለማደግ ጥሩ የሆነ መሠረት ያስፈልገናል። ይኸውም ሌላውን ሳይሆን ራሳችንን ሆነን መገኘት ነው። ራሳችንን ከመለወጥ ይልቅ ራሳችንን ሆነን እንድናድግ የሚረዱንን ብዙ ጠቃሚ ምክሮችን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አስፍረናል። የብዙዎች ጥያቄ "ሰው ራሱን የማይጠላ ከሆነ፣ ሌላውን ለመሆን ለምን ይሞክራል?" የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆን በማሰብ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንዳንድ ጠቃሚ



የሆኑ ሃሳቦች ተዘርዝረዋል። "እውነት" የሆነውን ጌታ ለመከተል እውነተኛ መሆንን ይጠይቃል።

ከክርስቶስ ጋር ተቀራርበን ለመጓዝ ውሳኔ ማድረጋችን ጥሩ ጅማሬ ነው። ይህን ከእርሱ ጋር የጀመርነውን መንፈሳዊ ጉዞ በጥሩ ለመጨረስ፣ እርሱን እየመሰልን እንጂ፣ ሌላውን መስለን በማደግ አይደለም። በመንፈሳዊ ጉዟችን ላይ ከፍታም ሆነ ዝቅታ፣ ደስታም ሆነ ሀዘን፣ ሣቅም ሆነ ለቅሶ፣ ሽንፈትም ሆነ ስኬት በየቀኑ ያጋጥመናል። በእነዚህ ውስጥ አሸናፊ የሆነ ሕይወት መኖር የምንችለው ሌላውን ሳይሆን ራሳችንን ሆነን ነው። ያለንበትን መንፈሳዊ ይዞታ ለማወቅ፣ በቅድሚያ ራሳችንን እንደሚገባው ማወቅ አለብን። እውነተኛውን እኛነታችንን ስናውቅ፣ ለሚጠብቀን ትግል ራሳችንን የበለጠ ለማዘጋጀት ይረዳናል። ይሄም የሌላው ሰው ካርቦን-ኮፒ ከመሆን ይጠብቀናል። በእኛ ውስጥ መልካሙን ነገር መሥራት የጀመረው ጌታ ከፍጻሜ እንደሚያደርሰው እየተረዳን እንመጣለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ እውነት ሲገልጽ፦

- *"በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍጻሜው እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ" ይላል (ፊልጵ. 1፥6)።*

በዓለም ላይ እውነት ሳይሆኑ፣ እውነት የሚመስሉ ብዙ ነገሮች እንዳሉ የታወቀ ነው። ወርቅ ሳይሆኑ፣ ወርቅ የሚመስሉ፣ እውነት ሳይሆኑ እውነት መሳይ እምነቶች ብዙ አሉ። በየትኛውም አገር እውነት ያልሆነ መቶ ብር አትሞ መጠቀም ወንጀል ነው። ይህን ዓይነቱን ወንጀል መፈጸም ከፍተኛ ቅጣት እንደ ሚያስቀጣ እያወቅን ራሳችንን ለአደጋ አጋልጠን እንደማንሰጥ የታወቀ ነው። እውነት ያልሆነ መቶ ብር፣ እውነተኛ ብር መስሏቸው ሰዎች ሳያውቁ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ሊገበያዩበት ይችላሉ። ገበያ ውስጥ ዞሮ ዞሮ መጨረሻ ላይ ባንክ ሲደርስ ግን፣ የባንክ ባለሞያዎች እውነተኛ መቶ ብር አለመሆኑን በቀላሉ አው ቀው፣ እንደገና ሰዎች እጅ እንዳይገቡ ሁሉንም ሰብስበው በእሳት ያቃጥሏቸዋል።

እውነት መሳይ ዕቃ እንዳለ ሁሉ፣ እውነት መሳይ ክርስትናም አለ። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስቲያን የሚመስሉ በብዛት ይገኛሉ። ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌላ ሰው ለመሆን የሚሞክሩ፣ እውነተኞች ሳይሆኑ እውነት የሚመስሉ (ካውንተርፌት) ክርስቲያኖች፣ እንዲሁም እውነተኛ አገልጋዮች ሳይሆኑ እውነት መሳይ አገልጋዮች የበዙበት ዘመን ነው። ያልሆኑትን መስለው ሰውን መዋሸት ይችላሉ። እግዚአብሔርን ግን መዋሸት አይችሉም። አንዳንዶች ደግሞ እውነተኛ ክርስቲያኖች፣ እውነተኛ አገልጋዮች ቢሆኑም እንኳን፣ ከሌላው በልጠው ወይም ተልቀው ለመታየት ሲሉ ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌላውን ለመምሰል የሚሞክሩ አሉ። ያልተረዱት ነገር ቢኖር ግን፣ ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌላውን ለመሆን ሲሞክሩ "እውነትነት የሌለው" የክርስትና ሕይወት እየኖሩ መሆናቸውን ነው።

በመንፈሳዊው ዓለምም፣ ማንም ሳያውቅብን መስለንና አስመስለን መኖር እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ መጨረሻ ላይ ሁሉን በሚያውቀው ጌታ ፊት ስንቀርብ፣ እውነተኛው ማንነታቸው ይገለጣል። ለምሳሌ ራሴን ሆኜ፣ እግዚአ ብሔር በሰጠኝ መንፈሳዊ ስጦታ ተጠቅሜ በማገልገል ፈንታ፣ እግዚአብሔር ያላደረገውን "አደረገ"፣ ያልተናገረውን "ተናገረ"፣ ያልፈወሰውን "ፈወሰ" ብዬ፣ ቤኒ ሒንን መስዬ መኖር እችላለሁ። ከጌታ እጅ ሽልማቴን ለመቀበል በእግዚአብሔር ፊት ስቀርብ፣ በእርሱ ፊት ምንም ነገር መሰወር ስለማይችል፣ "አንተ መለሰ ወጉ አይደለህም እንዴ? ይህን ሽልማት ልሰጥህ የነበረው እኮ ቤኒ ሂንን መስለሽኝ ነው" ቢለኝስ?

እኔ "ቤኒ ሒንን" ለመሆን ስታገል፣ "መለሰ ወጉን" ሳልሆን ብቀር፣ ተጠያቂ አልሆንም ወይ? ራሴን ሳልሆን፣ በሰጠኝ ስጦታ ሳልጠቀም፣ "አድርግ" ያለኝን ሳላደርግ ብቀር ትልቅ ኪሳራ አይሆንብኝም ወይ? ቤኒሒንን መስዬ ለብዙ ሕዝብ ከምሰብክ፣ "መለሰ ወጉን" ሆኜ ለጥቂት ሰው ብሰብክ ይሻለኛል። እራሴን ሆኜ ማገልገሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት የበለጠ ፍሬያማ ያደርገኛል ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ እግዚአብሔር "ቤኒ ሒንን" ሳይሆን፣ "መለሰ ወጉን" አድርጎ



የሠራኝ አምላክ ስለማይሳሳት፣ መለሰ ወጉን መሆን ይሻለኛል። እግዚአብሔር እኔን ከቤኒ ሒን ጋር አያወዳድረኝም። "ለምን ቤኒ ሒንን አልሆንክም?" አይለኝም። ይህ መጽሐፍ ሌላውን ከመምሰል፣ ኢየሱስን እንድንመስል፣ ራሳችንን ከማንም ጋር እንዳናወዳድር ይመክራል።

እግዚአብሔር ግብዝነትን፣ ይኸውም ያልሆኑትን እንደሆኑ ማስመሰልን በጣም ይጠላል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ከነበሩት መንፈሳዊም ሆነ የፖለቲካ ዕንቅስቃሴዎች መካከል "ፈሪሳውያን" የተባሉትን በጣም ይቃወማቸውና በኃይለኛ ቃል ይናገራቸው እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። ፈሪሳውያንን ከጠላበት ምክንያት አንደኛው ግብዝነታቸውን፣ ያልሆኑትን መስለው ለመታየት መሞከራቸውን ነው። በክርስቶስ ዘመን በተለያየ ስም የሚጠሩ ፈሪሳውያን ነበሩ። በእኛ ዘመን ያሉት ፈሪሳውያን ግን ስም አይውጣላቸው እንጂ፣ የተለያየ መልክና አቋም ያላቸው ፈሪሳውያን እንዳሉ የታወቀ ነው።

በዘመናችንም "ጥቅም፣ የከበሬታ ወንበር ፈላጊ ፈሪሳውያን" አሉ። እርግጥ ነው እንደ ጥንቶቹ በቀላሉ እነርሱን መለየት አይቻልም። በአለባበሳቸው እንደ ጥንቶቹ "የልብሳቸውን ዘርፍ አያስረዝሙም"፤ በሥርዓት አጠባበቃቸውም የጥንቶቹን "ጥቅም ፈላጊ ፈሪሳውያንን" አይመስሉም። ይሁን እንጂ፤ በባህሪያቸው በጣም እነርሱን ይመስላሉ። የወንጌልን አገልግሎትን ለራሳቸው ጥቅም የሚያውሉና ሳይታወቅባቸው ክብርን፣ ዝናንና ብልጽግናን ለማግኘት የሚሮጡ ናቸው። "የራሳቸውን ክብር" የሚመቱና የሚያስመቱ፣ እግዚአብሔር ያላደረገውን "አደረገ"፣ ያልሆነውን "ሆነ"፣ ያልተፈጸመውን "ተፈጸመ" በማለት የሚያወሩና የሚያስወሩ ናቸው። እነርሱን እስከጠቀማቸው፣ ክብርና ዝናን እስካስገኘላቸው ድረስ፣ "ታየን፣ ተገለጠልን" በማለት በሌሎች ሕይወት ውስጥ ለሚያመጡት ችግር ፈጽሞ ግድ የሌላቸው አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፀጋ ስጦታዎች የሚናገረውን ለራስ ጥቅም እንዲመች በማድረግ እውነትነት በሌለው፣ ይኸውም "በተአምር፣ በትንቢትና በመገለጥ ስም" የብዙዎችን ሕይወት ለመጉዳት ምክንያት ሆነዋል። በአሁኑ ጊዜ በየዋህ ክርስቲያኖች ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ቀላል አይደለም።

የዘመኑ *“ፈሪሳውያን”* በአዲስ ኪዳን ዘመን ከነበሩት የከፋ የሚያደርጋቸው፣ የራሳቸው የሆነ እውቀትም ሆነ አቋም የሌላቸው መሆኑ ነው። ከዚህ የተነሳ ያዩትን ሁሉ መሆን ያምራቸዋል። አንድ አገልጋይ የሚያስተምረው ትምህርት፣ የሚለማመደው ልምምድ ልክ ይሁን አይሁን መለየት ስለማይችሉ፣ ዝናና ስም የሚያስጣቸው ከሆነ፣ መኮረጅ ብቻ ሳይሆን፣ ትምህርቱን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ወስደው እንደ ራሳቸው አድርገው ያስተምሩታል፤ ይለማመዱታል።

የዘመኑ “ፈሪሳውያን” እንደ ጥንቶቹ ፊታቸውን በሻሽ ሸፍነው ባይሄዱም፣ በእኛም ዘመን እነርሱን የሚመስሉ መኖራቸው የታወቀ ነው። የጥንት ፈሪሳውያን፣ ሴት በአጠገባቸው ስታልፍ ተሳስተው እንዳያዩ በማለት ዓይናቸውን ጨፍነው ስለሚሄዱ፣ እንቅፋት እግሮቻቸውን እያቆሰለውና እየደሙ የሚኖሩ በመሆናቸው *“ደንቃፋ ፈሪሳውያን”* የሚል ተጨማሪ ስም ተሰጥቷቸው ነበር። በሰው ዘንድ ለመታየት ዓይናቸውን በመጨፈን ጨዋ ይምሰሉ እንጂ፤ ልባቸውና ድርጊታቸው ግን ንጹህ አልነበረም። እንደ ጥንቶቹ የዘመኑ ፈሪሳውያን “ዓይኖቻቸውን ጨፍነው” የሚሄዱ ሳይሆኑ፣ በትክክል ማሰብ እንዳይችሉ ሆን ብለው አንጎላቸውን የሚጨፍኑ ናቸው። እግዚአብሔር በሰጣቸው አዕምሮ መጠቀም “ኃጢአት” ይመስላቸዋል። መማርን፣ ማወቅን *“መንፈሳዊነት የሌለው”* ወይም ኃጢአት እንደሆነ አድርገው ስለሚመለከቱ፤ ባለመማራቸው ይኮራሉ። አለመማር ክብር ሳይሆን ውርደት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር የተረዱት አይመስልም።

- *“ትምህርት የማይወድ ሰው ድህነትና ውርደት ይገጥመዋል”* ይላል (ምሳሌ 13፣18)።

ዕውቀትን የሚጠሉትን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ፥

- *“እናንተ ሞኞች! እስከ መቼ ሞኝነትን ትመርጣላችሁ በዕውቀትስ ላይ በማፌዝ ደስ የሚላችሁ እስከ መቼ ነው? እስከ መቼ ዕውቀትን ትጠላላችሁ?” ብሎ ይጠይቃቸዋል* (ምሳሌ 1፣22)።



የጥንቶቹ ፈሪሳውያን ዓይናቸውን በመጨፈናቸው ምክንያት የሚቆስለው እግሮቻቸው ብቻ ነበር። የዘመኑ *“ደንቃፋ ፈሪሳውያን”* ግን ጉዳት የሚደርስባቸው በአንዱ የሰውነት ክፍላቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ ሕይወታቸው ነው። ያ ብቻ አይደለም። እነርሱ በሚያደርጉት፤ ጥበብ በጎደለው ውሳኔያቸውና ድርጊታቸው ምክንያት የሚቆስሉት፣ የሚደሙት እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ ቤተሰቦቻቸውም ጭምር ናቸው። ሠርተው በመብላት ፈንታ፣ እግዚአብሔር ሳይጠራቸው *“ጠራኝ”* በማለት ያለሥራ የትም ሲንከራተቱ ቤተሰቦቻቸውን ያስርባሉ።

በቅድስና ለመኖር ራሳቸውን የሚያስጨንቁ አይደሉም። ይሁን እንጂ፣ ራሳቸውን አተልቀው፣ ከሌሎች የተሻሉ አድርገው የሚመለከቱ ናቸው። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም ራስን የማተለቅ ችግር ስለነበረባቸው፣ ለእነዚያ በእግሩ ሥር ለተማሩት፣ ኩሩዎች፣ “ከተራው ምዕመናን እንበልጣለን” ብለው ራሳቸውን ለሚገምቱ ደቀ መዛሙርቱ አደገኛነቱን የተረዳው ጌታ *“ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁ”* ሲል ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸዋል። ይህን ሲሰሙ በወቅቱ  የክርስቶስ አባባል ትንሽ ግራ ሳያጋባቸው እንዳልቀረ እንገምታለን። ቢሆንም *“በአለባበሳችን፣ በመልካችን፣ በትምህርታችን፣ በዘራችን፣ ሌላው ቀርቶ በእምነታችንም ከሌሎች እንበልጣለን፣ ከሌሎች የተሻልን ነን”* በማለት ራሳቸውን አሳድገው ሌሎችን አሳንሰው የሚያዩ ፈሪሳውያን ነበሩ። በእኛም ዘመን አሉ።

የጥንት ፈሪሳውያን እውነተኑት የሌለውን ዓይነት ትሕትና ያሳዩ እንደነበረ የታወቀ ነው። የዘመኑ ፈሪሳውያንም፣ ትሕትናን ራሳቸውን የሚያሳዩበት አድርገው በመጠቀም፣ *“የተቀለበሰ ትሕትና”* ለማሳየት ይሞክራሉ። *“ጌታ ከሁሉ በታች የሆንኩትን፣ ...ከትል የማንሰውን፣ ዕውቀት የሌለኝን፣ ከስምንተኛ ክፍል በላይ ያልተማርኩትን፣ እንግሊዝኛ መስማትም ሆነ መናገር የማልችለውን፣ ከውርንጭላ የማንሰውን፣ በአህያ የተናገረው አምላክ የክብሩ መግለጫ አደረገኝ”* ይላሉ። ይህን ዓይነቱ አነጋገር ትሁት መሆናቸውን ሳይሆን፣ አስመሳይነታቸውን የሚገልጽ ነው። ያልሆኑትን ሆኖ መታየት እውነተኛው እኛነታችን እስኪገለጥ

ድረስ፣ ለጊዜው የሚጠቅም ይምሰል እንጂ፣ የሕሊና ጭንቀት ያስከትላል። ይህም ሃሳብ በሰፊው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተገልጿል።

ብዙዎች ራሳቸውን እንዳሉ መቀበል የሚያቅታቸው፣ ራሳቸውን ከሌላው ጋር ስለሚያወዳድሩ እንደሆነ ግልጽ ነው። ሰው ሁሉ የራሱ የሆነ ብርቱና ደካማ ጎን አለው። ይህንን እውነት ባለመገንዘብ ራሳችንን ከሌላው ጋር ማወዳደር፣ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ራሳችንን ከሌላው ጋር ስናወዳድር ያነስን ወይም የተበለጥን ከመሰለን፣ የዋጋቢስነት ስሜት የሚሰማን መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በበለጡን ሰዎች ላይ የመራራነትና የጥላቻ መንፈስ ሊጠናወተን እንደሚችል የታወቀ ነው። ሁልጊዜ ከእኛ የተሻሉ ወይም ከእኛ የበለጡ ሰዎች ሲያጋጥሙን፣ የዝቅተኛነት ስሜት ያጠቃናል። ከእኛ ያነሱ ሰዎች ሲያጋጥሙን ደግሞ፣ የበላይነት ስሜት ይሰማናል። እንዲሁም አድገን ያበቃን፣ ወይም ከዕድገት መሰላል መጨረሻው ጫፍ ላይ የደረስን ይመስለንና የበለጠ ለማደግ አስፈላጊውን ጥረት እንዳናደርግ ዕንቅፋት ይሆንብናል።

- *ራሳችንን ከሌላው ጋር ማወዳደር፣ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ራሳችንን ከሌላው ጋር ስናወዳድር እንደጠበቅነው ሆኖ ካላገኘነው ልባችን በሀዘንና በመራራነት የተሞላ ይሆናል። ሁልጊዜ ከእኛ የሚበልጡና ከእኛ የሚያንሱ ሰዎች እንዳሉ ማወቅ አለብን።*
- *ራስን ከሌላው ጋር ማወዳደር የተስፋ መቁረጥና የመደናገጥ መንገድ፣ እንዲሁም ጊዜንና ጉልበትን ማባከን ይሆናል።*
- *ስኬት የምናገኘው ጥሩ አድርገን ሥራችንን በመሥራት እንጂ፣ ሌሎች ምን ይሠሩ ይሆን ብለን በመጨነቅ የሚገኝ አይደለም።*
- *ሽንፈትም ሆነ ስኬት ያለው በእኛ እጅ ነው። የሌላው ስኬት፣ የእኛን ስኬት አያጨናግፍም።*
- *ውሳኔ የምናደርገው እኛ በምንፈልገው ነገር እንጂ፣ ሌሎች እንዲሆንልን በሚፈልጉት ላይ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን።*



*"ደሀና ነኝ፤ ነገር ግን መሆን ከሚገባኝ ደረጃ ላይ ገና አልደረስኩም" እንላለን ወይስ ራሳችንን ከሌላው ጋር በማስተያየት፣ "ይሀን ያህል ከሌሎች የባሰ መጥፎ አይደለሁም" እንላለን?*

በዚህ ዓይነት ራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደር፣ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ራስን ከሌላው ጋር ስለ ማወዳደር ሰፊ ዳሰስ ተደርጎበታል። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን *"ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠበቁ"* ሲላቸው በአጠቃላይ እውነትነት የሌለው፣ ካርቦን-ኮፒ የሆነ ሕይወት እንዳይኖሩ መምከሩ ነው። ይህን ዓይነቱ ማስጠንቀቂያ በጥንት ዘመን ለነበሩ አማኞች ብቻ ሳይሆን፣ በአሁኑ ዘመን ላለነው አማኞችም በጣም አስፈላጊ ነው። እንደ ጥንት ፈሪሳውያን *"እግዚአብሔር ሆይ! እንደ ሌሎች ሰዎች ደካማ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ"* እያልን የራሳችንን ጽድቅ በመቁጠር፣ ያልሆነውን መስለን እንዳንኖር እግዚአብሔር ይርዳን። ይህቺ አነስተኛ መጽሐፍ ለጥያቄያችሁ ሁሉ መልስ ትሰጣለች ብዬ ሳይሆን፣ በመጠኑም ቢሆን አንዳንድ እውነቶችን ትገልጣለች ብዬ ለአንባቢያን አቅርቤአለሁና ተጠቀሙበት። ሰውን ሳይሆን ቅዱስ የሆነውን ጌታ ኢየሱስን እንድንመስል እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን። አሜን!

*መለሰ ወጉ፣*

1

# ሁላችንም አንድ ዓይነት ሆነን አልተፈጠርንም

*"ያልሆንነውን ሆነን ከምንወደድ፣ የሆንነውን ሆነን ብንጠላ ይሻላል"*

*–አንድሬ ጋይድ*

አንዳንድ ሰዎች ምንም ያህል ያማረ መልክና ቁመና፣ በጣም ተወዳጅ የሆነ ተፈጥሯዊ ባሕሪ ያላቸው ቢሆኑም፣ ስለራሳቸው ጥሩ የሆነ አመለካከት ወይም አስተያየት የላቸውም። ሰው ሁሉ የማይወዳቸው፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያጡ፣ በሥራቸው ብቃት የሌላቸው መስሎ ይሰማቸዋል። ይሁን እንጂ፣ ስሜታቸው በእውነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ባሉበት ሕብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው፣ ራሳቸውንና ኑሯቸውን አሸንፈው የሚኖሩ፣ የስንፍና ባሕሪ የማይታይባቸው ትጉህ ሠራተኞች ቢሆኑም፣ ሁልጊዜ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ይመለከታሉ። በተለይ ከእነርሱ የበለጠ የተሳካላቸውን ሰዎች ሲያዩ፣ ደስታቸው በቀላሉ ይጠፋል።

በኑሯቸው ከእነርሱ የተሻሉ ሰዎችን መመልከት፣ ከእነርሱ ትምህርት ለመቅሰም እስከ ሆነ ድረስ፣ *"እንዴት ከዚህ ደረሱ?"* ብሎ መጠየቅ፣ ይህን ያህል ክፉ አይደለም። ራሳቸውን ከሌሎች ጋር አወዳድረው የራሳቸውን ዝቅተኛነት ለማየት ከሆነ ግን፣ ይጎዳቸዋል እንጂ አይጠ

ቅማቸውም። አንዳንዶች ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በመመልከት *"የማልረባ ነኝ"* ብለው ስለ ደመደሙ፣ ሲሳካላቸው እንኳን ባገኙት ስኬት በመደሰት ፈንታ፣ *"የተሳካልኝ እንደ ዕድል፣ ወይም እንደ አጋጣሚ ሆኖ ነው እንጂ፣ ጥሩ ሠርቼ አይደለም"* ይላሉ። ችግራቸው እዚህ ላይ አያ ቆምም። ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ስለሚመለከቱ፣ የሆኑትን በመሆን ፈንታ፣ ሌሎች ከደረሱበት ለመድረስ የሌላው ሰው ካርቦን-ኮፒ ወይም ግልባጭ ለመሆን ይሞክራሉ።

## 1. በራስ እምነት ማጣት ከአስተዳደግ የሚመጣ ይሆን?

እኛ ሰዎች እርስ በርሳችን የምንመሳሰልባቸው ነገሮች አሉን። ይኸውም ሁላችንም፥

*የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል ነው።*

*ከሌሎች እንስሳትና አውሬዎች የምንለይባቸውም ነገሮች አሉን።*

*ሁላችንም ማሰብ፣ ሀሳባችንን በንግግር መግለጽ፣ እንዲሁም ማመዛዘን እንችላለን።*

*ሁላችንም የራሳችን የሆነ ስሜት፣ የራሳችን የሆነ ፈቃድ አለን። ደስ ሲለን እንስቃለን፤ የሚያሳዝን ነገር ሲያጋጥመን እናለቅሳለን።*

ከላይ በገለጽናቸው ነገሮች ላይ ሁላችንም ተመሳሳይነት አለን። ያሁን እንጂ፤ በተፈጥሮ ጠባያችን፣ በመልካችን፣ በቁመታችን እንዲሁም በአስተሳሰብ ችሎታችን የተለያየን እንጂ አንድ ዓይነት አይደለንም። ሁላ ችንም አንድ ዓይነት ብንሆን ኖሮ፣ ዓለም ምን ያህል የሚሰለች፣ ውበት የሌለው ሥፍራ ይሆን ነበር? እግዚአብሔር የተለያየ የተፈጥሮ ባህሪ ሰጥቶ የፈጠረን በመሆናችን፣ አንድ ዓይነት ለመሆን ለምን ሙከራ እናደር ጋለን?





## *2. ሰው በአንዳንድ ነገር ይመሳሰል እንጂ፣ በሁሉም ነገር አንድ ዓይነት አይደለም*

አንድ ዓይነት የሆኑ ሁለት ሰዎች በዓለም ላይ የሉም። እግዚአ ብሔር ሁላችንንም የተለያየን አድርጎ ነው የፈጠረን። የተለያየን አድርጎ ከፈጠረን፣ ታዲያ ሌላውን ለመምሰል ወይም የሌላው ሰው ግልባጭ ወይም ካርቦን-ኮፒ ለመሆን ጥረት የምናደርገው ለምን ይሆን? እውነተ ኛውን እኛነታችንን ሸፍነን ያልሆንነውን እንደሆንን አድርገን ራሳችንን ለምን እናሳያለን? በራሳችን እምነት በማጣታችን ምክንያት ይሆን?

- *ሊዩ ቡስካግሊያ የተባለው ጸሀፊ፣ "በዓለም ላይ ቀላሉ ነገር ራሳችንን መሆን ነው፤ ከባዱና አስቸጋሪው ነገር፣ ሌሎች እንድንሆን የሚፈል ጉትን ለመሆን ስንሞክር ነው። ሰዎች እነርሱ በሚፈልጉት ሁኔታ ውስጥ እንዲያስቀምጡን አንፍቀድላቸው"* አለ።

በብዙ አቅጣጫ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው የባረከው፣ ልዩ ልዩ ችሎታዎችን (ስጦታዎችን) የሰጠው ቢሆንም፣ በተሰጠው ጥበብና ዕውቀት ረክቶና ተደስቶ፣ እንዲሁም ራሱን እንዳለ ተቀብሎ ከመኖር ይልቅ፣ ራሱ ከሆነው ውጪ ሌላ ሰው ሆኖ ለመገኘት፣ ወይም ለመምሰል ከፍተኛ ጥረት የሚያደርገው ለምን ይሆን? ንግግሩ፣ አረማመዱ፣ አቀ ማመጡ የሚያደንቀው ሰው ያለውን ዓይነት እንዲመስልለት ለምን ይፈልጋል። ምክንያቱ ምን ይሆን? የሚያሳዝነው፤ ያ ኮፒ የሚያደርገው ሰው የተሳሳተ አቋም ያለው ቢሆንም፣ ስህተቱን እንዳለ ኮፒ የሚያደርግ መሆኑ ነው። ያለንበት ዘመን፣ ይህን ዓይነት ባህሪ ያላቸው ሰዎች በብዛት የሚታዩበት ዘመን እንደሆነ ለብዙዎች ስውር አይደለም። ሰዎች ራሳ ቸውን በመሆን ፈንታ፣ ለመሆን የሚፈልጉትን ሰው ኮፒ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም አይሳካላቸውም።

በሰለጠነው ዓለም የሚኖሩ ህጻናት ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ በቴሌ ቪዥን ስክሪናቸው በሚቀርብላቸው የተለያዩ የፊልም ተዋንያኖች አዕም ሯቸው የተሞላ በመሆኑ አድገውም ሆነ፣ አሁን ባሉበት የዕድሜ ደረጃ ውስጥ ሆነው "ማንን መምሰል፤ ወይም ማንን መሆን ትፈልጋላችሁ?"

ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ፣ “ራሳችንን መሆን እንፈልጋለን” በማለት ፈንታ፣ አዕምሯቸውን ካጣበቡት የፊልም ተዋንያኖች መካከል የሚያደንቁትን የአንዱን የፊልም ተዋንያን ስም ይጠሩና “እከሌን መሆን እፈልጋለሁ” ይላሉ።

እግዚአብሔር በነፍስ ወከፍ እንጂ ፋብሪካ ውስጥ እንደሚሠራ ተራ ዕቃ ሰውን ሁሉ አንድ ዓይነት አድርጎ አልፈጠረውም። ሥጋ የለበሰ ሰው ሁሉ በአጠቃላይ የሚመሳሰልበት ነገር እንዳለው ከላይ ገልጸናል። ከተቀሩት እንስሳት ልዩና የበላይ የሚያደርጉት ፈጣሪ ከሆነው እግዚአ ብሔር ያገኘው መለያ የሆኑ ባሕሪያት (attributes) አሉት። በማንነቱ ሰው ሁሉ ይመሳሰላል። ይኸውም የሚያስብ፣ የሚያመዛዝን፣ ስሜት ያለው፣ የራሱ ፈቃድ ያለው ወዘተ. ነው። በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት ነገሮች ሰው ሁሉ ይመሳሰላል።

በሌላ በኩል ግን፣ አንዱ ከሌላው የሚለይበት የራሱ የሆነ መለያ፣ የራሱ የሆነ የተፈጥሮ ችሎታ፣ እንዲሁም የራሱ የሆነ ተፈጥሯዊ ባሕሪ እንዲኖረው አድርጎ የተፈጠረ እንጂ፣ አንድ ዓይነት የሆነ፣ ወይም የሌላው ሰው ካርቦን-ኮፒ ወይም ግልባጭ ሆኖ የተፈጠረ አይደለም። ዓለም አንድ ዓይነት በሆኑ ሰዎች የተሞላች አይደለችም። እያንዳንዱ ሰው ልዩ (unique) ነው። ራሳችንን ለመለወጥና ሌላውን ለመምሰል ስንሞክር ከላይ የገለጽነውን እውነት መካዳችን ይሆናል። እንዲሁም እግዚአብሔር ሰውን ግሩምና ድንቅ አድርጎ እንደ ፈጠረው፣ በሕይወቱ ዓላማውን መፈጸም የሚያስችለውን የተፈጥሮ ስጦታ እንደሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። ዘማሪው ስለዚህ እውነት ሲመሰክር፣ *“ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁ”* ይላል። እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ከጨረሰ በኋላ በእጆቹ ሥራ በጣም ደስ የተሰኘ መሆኑን ሲገልጽ፥

- *“እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ” ይላል (ዘፍ. 1፡31)።*

ይህንን እውነት ባለመረዳት፣ *“እኔ በሕይወቴ ውጤት-አልባ የሆንኩት፣ በኑሮዬ ያልተሳካልኝ፣ እግዚአብሔር እኔን ሲሠራኝ እንደሌሎቹ*





*የተፈጥሮ ስጦታ ወይም ችሎታ ሳይሰጠኝ ስለ ፈጠረኝ ነው”* በማለት በእግዚአብሔር ላይ የሚያማርሩ አንዳንድ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ከሌላው የተለየ አድርጎ ከፈጠረው፣ ታዲያ እንደተፈጠረው ራሱን በመሆን ፈንታ የሌላው ሰው ግልባጭ ወይም ካርቦን-ኮፒ ለመሆን ለምን ይሞክራል? ይሄ የብዙዎቻችን ጥያቄ ሳይሆን አይቀርም። የዚህም መጽሐፍ ትልቁ ዓላማ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው እጅግ መልካም አድርጎ የፈጠረው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የተፈጠረበትን ዓላማ መፈጸም እንዲችል የተፈጥሮ ችሎታ የሰጠው መሆኑን እናምናለን። ሰው እንዲሁ እንደ አጋጣሚ፣ ወይም በወላጆቹ የሥጋ ፈቃድ ወደዚህ ዓለም የመጣ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ እንደተፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፥

- *“ስለ እናንተ ያለኝን ዕቅድ የማውቅ እኔ ብቻ ነኝ፤ ይህም ዕቅድ ክፉትን ሳይሆን ሰላምን በማስገኘት እናንተ በተስፋ የምትጠብቁት መልካም ነገር የሚፈጸምበት ነው” ይላል (ኤር. 29፡11)።*

የሰውን ሁለንተና የፈጠረ፣ ገና በእናቱ ማሕጸን ውስጥ ሳለ አንግጥጥሞ የሠራው ኃያሉ አምላክ፣ ለፈጠረው ሰው ሁሉ ዓላማና ዕቅድ እንዳለው ቃሉ በግልጽ ይመሰክራል። ዘማሪው፣

- *“ሁለንተናዬን የፈጠርህ አንተ ነህ፤ በእናቴ ማሕፀን አንግጥጥመህ የሠራኸኝ አንተ ነህ። ክብር የሚገባህ ስለሆንህም አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ሁሉ ግሩምና ድንቅ ነው፤ ጠንቅቄም ዐውቃለሁ። አጥንቶቼ በመሠራት ላይ እንዳሉ በእናቴ ማሕፀን በጥንቃቄ በመገጣጠም እንዳሉ፣ እዚያም በስውር በማድግበት ጊዜ፣ በዚያ መሆኔን አንተ ታውቅ ነበር” ይላል (መዝ. 139፡13-15)።*

ለመሆኑ እኔና እናንተ ልክ እግዚአብሔር እንደፈጠረን ነን? ወይስ የሌላው ሰው *ካርቦን-ኮፒ ወይም ግልባጭ ለመሆን እየሞከርን ነው? አስመሳዮች (phony) ነን?* ወይስ “እውነተኞች” (authentic) ነን? “እውነተኛነት” በሕይወታችን የሚዳብረው በሂደት ስለሆነ፣ በእርግጥ ሁላችንም ፍጹም ከሆነ “እውነተኛነት” ደረጃ ገና አልደረስንም። መጠኑና ዓይነቱ የተለያየ

ይሁን እንጂ፣ ሁላችንም የራሳችን የሆነ “አስመሳይነት” አለን። እግዚአብሔርን ደስ ከሚያሰኙት ነገሮች መካከል አንደኛው፣ እኔና እናንተ ማንነታችንን ሳንለውጥ፣ ልክ እርሱ እንደፈጠረን ሆነን መገኘት ስንችል ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆን፣

- *ውጪያችንና ውስጣችንን በደንብ በሚያውቀው አምላክ ፊት ሌላውን ሳይሆን እራሳችንን ሆነን መቅረብ አለብን)።*
- *እግዚአብሔር የጸጋ አምላክ ስለሆነ፣ ልክ እንዳለነው ስለሚቀበለን፣ እርሱን ለማስደሰት ራሳችንን ለውጠን፣ ወይም ራሳችንን አሳምረን መቅረብ እንደማያስፈልገን ማወቅ አለብን፣*
- *እውነተኛውን ማንነታችንን ለመሰወር ፊታችን ላይ ያደረግነውን መሸፈኛ (ማስክ) ከፊታችን ላይ ማንሳትና፣ በእግዚአብሔር ፊት እውነተኞች ሆነን መቅረብ አለብን።*

አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን ለመሸፈን ከፊታቸው ላይ ያለውን ማስክ ወይም ሽፋን አንስተው እውነተኛ ሆነው መቅረብ የሚፈሩበት ዋናው ምክንያት ለምን ይሆን? ሰዎች እውነተኛውን ማንነታቸውን ካወቁ የማይወዷቸው፣ እንዲሁም እግዚአብሔር የማይቀበላቸው ስለሚመስላቸው ነው። ያልተረዱት እውነት ቢኖር ግን፣ ሰው ራሱን ለመደበቅ ይሞክር እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ዓይን መደበቅ የሚችል ማንም ሰው እንደሌለ ነው። እግዚአብሔር የውጪውን ብቻ ሳይሆን የውስጡንም ማየት ይችላል። እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፣ ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት የሚኖረን፣ በእግዚአብሔር ፊት እውነተኞች ሆነን መቅረብ ስንችል ብቻ ነው።

ዛሬ ብዙዎች እውነተኛውን “እነርሱነታቸውን” ስለሚደብቁ፣ ራሳቸውን ማወቅ ያቃታቸው ይመስላሉ።

> *አንድ ጊዜ በአዕምሮው የተናወጠ አንድ ሰው ዋሽንግተን ዲ. ሲ. ውስጥ ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ገብቶ፣ ፋይሊንግ ካቢኔቱን በኃይል እየከፈተ፣ ውስጡ ያሉትን ወረቀቶች ይቀድና ያተረማምስ ነበር። የሠራተኞችን ዴስኮችን እየከፈተ*





> *አንድ ነገር ይፈልግ ነበር። ይህንን የተመለከቱ አንዳንድ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች “ምን እያደረግህ ነው? ምንድነው የምትፈልገው?” ብለው ጠየቁት። “እኔ እራሴን እየፈለግሁ ነው” አላቸው። ታሪኩ ቀልድና የሚያስቅ ይምሰል እንጂ፣ ጥሩ ትምህርት ይዟል። አንዳንዶቻችን በሚያሳዝን ሁኔታ እኛነታችንን ያጣን በመሆናችን የግድ ራሳችንን ማግኘት አለብን።*

ሰው ራሱን ምንም ያህል ቢወድ፣ ሌላውን ሰው ለመሆን ወይም ለመምሰል ጥረት የሚያደርገው ለምን ይሆን? ሰው ከራሱ ውጪ ምንም ማድረግ ስለማይችል፣ መውሰድ ያለበት እርምጃ ቢኖር ራሱን ልክ እንዳለ መቀበል ብቻ ነው። ሳናሳንስና ሳናተልቅ ልክ እንዳለነው ራሳችንን እንይ፤ ልክ እንዳለነው ራሳችንን እንቀበል። እርግጥ ነው ራሳችንን ዘለቅ ብለን ስናይ፣ የማንወደው ነገር ይኖር ይሆናል። ቢሆንም ከራሳችን ውጪ ምንም ማድረግ ስለማንችል፣ ልክ እንዳለነው ራሳችንን የግድ መቀበል አለብን። ብዙ ጊዜ ራሳችንን አሳንሰን ስለምናይ፣ ራሳችንን መሆን አንፈልግም። ከራሳችን ጋር ለመስማማት፣ በውስጣችን በምናየው መልካም ባልሆነ ነገር ከራሳችን ጋራ ከምንጣላ ይልቅ፣ ለራሳችን ሥፍራ እንስጠው። ስለ ራሳችን ማወቅ ያለብን አንዳንድ እውነት አለ። ይኸውም፦

- *በዓለም ውስጥ እያንዳንዳችን አስፈላጊዎች ስለሆንን ራሳችንን ዝቅ አድርገን ማየት የለብንም።*
- *ዘላለማዊ የሆነ ዋጋ ያለን በመሆናችን፣ ምንም ነገር ቢደርስብን ዋጋችንን ሊቀንስ የሚችል ነገር የለም።*
- *በሰባዊነታችን ፍጹሞች አይደለንም፤ እንዲሁም ክፉዎችም አይደለንም።*
- *ለአደጋ የተጋለጥን ስለሆንን፣ በሕይወት እስካለን ድረስ ጉዳት ሊደርስብን ይችላል።*
- *ከአካባቢያችንና ከሁኔታዎች ጋር በማይለይ ሁኔታ የተያያዝን ስለሆንን፣ ከራሳችን ሮጠን ማምለጥ አንችልም።*

- *ሰዎች የሁኔታዎች ምክንያት ናቸው፤ ሁኔታዎችም በሰዎች ላይ ተጽዕኖን ያሳድራሉ። የእኛ መኖር ሁኔታዎችን ልዩ ማድረግ ይችላል።*
- *ተጠያቂ መሆን ጤናማነት ስለሆነ፤ አዎንታዊ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል።*

## *2. ሰው የሚታይና የማይታይ መልክ አለው*

ማንኛውም ሰው ሁለት ዓይነት መልክ አለው። ይኸውም፣ አንደኛው ውጫዊ የሆነ፣ ሰው ሁሉ ሊያየው የሚችለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ውስጣዊ የሆነ፣ ሥጋ ለባሽ የሆነ ሰው ሊያየው የማይችለው እውነተኛው እርሱነቱ ነው። አንዳንዶች ሰው እንዲያውቃቸው የሚፈልጉት በእውነተኛው ማንነታቸው ሳይሆን፣ ራሳቸውን ቀባብተውና አሳምረው በሚያቀርቡት እነርሱነታቸው ነው። ለዚህ ጥሩ ትምህርት እንዲሆነን አንዲት ሴት የተናገረቸውን እንደ ምሳሌ አቅርበንላችኋል።

> *አንድ ባልና ሚስት በቅርቡ ቤት ገዝተው የገቡትን ጎረቤቶቻቸውን ሄደው "እንኳን ደህና መጣችሁ" ለማለትና ለመተዋወቅ ፈልገው ሲዘጋጁ ሚስትየዋ ብዙ ሰዓት ፈጀች። ጸጉሯን ስትሠራ፣ ከንፈሯንና የጣቶቿን ጥፍር፣ እንዲሁም የዓይኖቿን ሽፋሽፍት ቀለም ስትቀባ ብዙ ጊዜ ወሰደች። መኪና ውስጥ ቁጭ ብሎ የሚጠብቃት ባሏ ትዕግሥቱ አልቆ፣ በቁጣ "አንቺ ሴትዮ! ምን ነካሽ? አትወጪም እንዴ? ይህን ያህል ጊዜ የምትፈጂው ምን እያደረግሽ ነው?" አላት። ሚስትየዋም ስትመልስለት፣ "ውዱ ባለቤቴ! እነዚህን ሰዎች ስናገኛቸው የመጀመሪያችን ጊዜ ነው። እውነተኛውን እኔነቴን እንዲያዩ ብዬ ነው" አለችው።[2]*

[2] Charles H. Gibboney. Living Beyond Your Means, Quality Printers, Bristol, VA. 1983.





ከላይ ታሪኳን ያነበብነው ሴት *"እውነተኛ" (authentic)* የሆነው ቁመናዋ፣ እርሷነቷን የሚገልጸው፣ ምንም ዓይነት ማስመሰል የሌለበት ውስጣዊው መልኳ እንደሆነ የተረዳችው አይመስለንም። ማጌጥ ደካማነት ነው ማለታችን ሳይሆን፣ ቀባብተን የምናሳየው መልክ እውነተኛውን እኛነታችንን ሊያሳይ አይችልም ማለታችን ነው። እውነተኛ የሆነ *ገጸ-ባሕሪ (character)* ያለው ሰው ሁለት ዓይነት መልክ ያለው፣ ይኸውም ከውጪ አንድ ዓይነት መልክ፣ ከውስጥ ደግሞ ሌላ ዓይነት መልክ ያለው ሳይሆን፣ ከውስጥም ሆነ ከውጪ አንድ ዓይነት የሆነ ነው። የሆንነው ሆነን ስንገኝ፣ ማስመሰል የሌለበት፣ በሕይወታችንና በአኗኗራችን *"እውነተኛ" (ኦቴንቲክ)* ሆነን መገኘታችን ነው።

- *ኦሴንቲክ (authentic) የሚለውን ቃል የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት "ጎኝ ያልነውን 'ሆነን መገኘት'–ቃላችንና ተግባራችን አንድ ዓይነት የሆነ ወይም እርስ በርሱ የማይቃረን ማለት ነው" ይለዋል።*

*"እውነተኝነት የሌለው" (inauthenticity)* ሰው፣ *"ጎኝ!"* ያለውን ሆኖ የማይገኝ ሰው ማለት ነው።[3] ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የሚያጋጥማት ተግዳሮት አማኞች *"እውነትነት የሌለው"* የክርስትና ሕይወት መኖራቸው ነው። ይኸውም ሕይወታቸውና አኗኗራቸው *"ጎን"* ከሚሉት ጋር አብሮ የማይሄድ ወይም የሚቃረን መሆኑ ነው። ***"ጥሩ ስም፤ ወይንም ዝና (reputation)"*** —ሰዎች ስለ እኛ በሚሰጡት አስተያየት ላይ የተመሠረተ ነው።—(what other people think of us). "ዝና" በውጤት መቃናት፣ በከፍተኛ ክንውን ላይ የተመሠረተ እንጂ፣ ብዙ ጊዜ ሆነን በተገኘነው እውነተኛው እኛነታችን ላይ የተመሠረተ ላይሆን ይችላል። ሰው የምናደርገውን አይቶ የሚሰጠን አስተያየት ወይም ግምት ነው። *"ገጸ-ባሕሪ" (character)* ሰው በማያየን ጊዜ የምናደርገው ሲሆን፤ *"ጥሩ ስም ወይም ዝና" (reputation)* ግን ሰው እያየን በምናደርገው ነገር የሚገኝ ውጤት ነው። "ጥሩ ስም" (ዝና) የምናገኘው ሰዎች በሚያዩት ውጪያዊ አቋማችን ስለሆነ፣ ብዙ ጊዜ ውስጣዊ ሕይወታችንን ችላ

[3] Bill Hybels. Honest To God, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI, 1990.

ብለን፣ ውጪያዊ ሕይወታችንን ለማሳመር፣ መስለን ለመታየት ከፍተኛ ጥረት ስናደርግ እንታያለን።

በአንድ ወቅት አንድ ኮንፍራንስ ላይ ከተናጋሪዎቹ መካከል አንደኛው፣ ማስተማሩን እንደ ጀመረ ከእርሱ ቀጥሎ የሚሰብከውን ሰው ስም ሳይጠቅስ በተዘዋዋሪ በትምህርቱ መንካት ጀመረ። የተነቀፈው አስተማሪ ደግሞ በጣም ተበሳጭቶ ስለ ነበረ የማስተማር ተራውን ሲያገኝ፣ ቀደም ሲል ለተናገረው ሰባኪ ኃይለኛ መልስ ለመስጠት ሞከረ። አድማጩ ሕዝብ በሁለቱ አስተማሪዎች መካከል የተፈጠረው ግጭት ገብቶት ለሁለት ተከፈለ። ይኸውም፣ አንደኛው ወገን የመጀመሪያውን ሰባኪ ሲደግፍ፣ ሌላው ወገን ደግሞ "እንኳን መልስ ሰጠልን" በማለት ሁለተኛውን ሰባኪ ደገፈ። የስብሰባው መንፈስ ወዲያ ተለወጠ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ሁለቱም ሰባኪዎች ጥልቀት ያለው "መንፈሳዊ ነገር" ለማስተማር እየሞከሩ ነበር። በዚህ ዓይነት የመጀመሪያው ክፍል ጊዜ አልቆ እረፍት ሆነ።

ሁኔታው ያላስደሰተው የኮንፍራንሱ መሪ ሁለቱን ተናጋሪዎች ለማስታረቅ ለብቻ ወስዶ ማነጋገር ሲጀምር፣ የመጀመሪያው ተናጋሪ ተበሳጭቶ ሁለተኛውን ሰባኪ፣ "አሁን መስበክህ ነው? አስታወክ እንጂ" በማለት ነቀፈው። በዚህ ዓይነት ሁለቱም የሚቀጥለውን ስብከታቸውን እንዲሰብኩ ዕድል ከተሰጣቸው ተራ በተራ መድረኩ ላይ ይሰዳደቡ ይሆናል በሚል ፍርሃት የፕሮግራሙ መሪ የሁለቱንም የማስተማር ፕሮግራም ሰርዞ ራሱ መልዕክቱን አቀረበ።

ስብከቱን ከማቅረቡ በፊት፣ "እኛ ክርስቲያኖች በፍቅራችን እንደምንታወቅ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ስለዚህ ከዚህ ቀጥለን 'አንድ ነን በመንፈሱ' የሚለውን መዝሙር እጅ ለእጅ ተያይዘን እንዘምር" በማለት ሕዝቡን ጠየቀ። በሁለቱ ሰባኪዎች መካከል ምንም ዓይነት ዕርቅ ሳይኖር፣ ሕዝቡ የተባለውን መዝሙር ዘመረ። ይሁን እንጂ፣ መንፈሳዊ መዝሙር መዘመሩ ብቻ ሁኔታው ተለወጠ ማለት አይደለም። የሁለቱም ተናጋሪዎች





ውስጣዊ ሁኔታ በቁጣና በመራራነት የተሞላ ሆኖ ውጪያዊ ፊታቸው ግን በፈገግታ የተሞላ ነበር። ሁለቱም ውስጣቸውን በሚያየው በእግዚአብሔር ፊት እውነተኞች አልነበሩም።

አንዳንድ ሰዎች የክርስትናን እምነት ከሚቃወሙበት፣ ወይም ከክርስቲያኖች የሚሸሹበት አንደኛው ምክንያት፣ ክርስቲያኖች የሚኖሩትን የግብዝነት ወይም የማስመሰል ሕይወታቸውን በመጥላት እንደሆነ ይናገራሉ። መድረክ ላይ የሚያሳዩትን ባሕሪ ከመድረክ ላይ ሲወርዱ አይኖሩበትም። ከላይ ያነበብነው ታሪክ የተለየ ነው። ብዙ ጊዜ እውነተኛው ማንነታችን መድረክ ላይ ተገልጾ አይታይም።

## 4. ሁላችንም መስሎ ከመታየት ነጻ አይደለንም፦

የታወቀው የሥነ ልቦና ምሁር፣ "ፍሪትዝ ፐርልስ" (Fritz Perls) የተዛባ የአዕምሮ አቋም ያለው ሰው በተለያየ የስሜት ደረጃ ውስጥ የሚያልፍ መሆኑን ይገልጻል።

- የመጀመሪያው "መስሎ የመታየት ደረጃ" (phoniness level) ይለዋል። በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው፣ ያልሆነውን እንደሆነ ለማስመሰል ይሞክራል። ይኸውም፣ ብርቱ፣ ታላቅ፣ ደስተኛ፣ እግዚአብሔር እርሱን ለዓለም የሰጠ ታላቅ በረከት ወይም ስጦታ እንደ ሆነ አድርጎ ራሱን ይመለከታል።[4]

በአሁኑ ጊዜ ያልሆኑትን እንደሆኑ አስመስለው ራሳቸውን የሚያቀርቡ ሰዎች የበዙበት ዘመን ነው። አንድ ጊዜ አንድ በጣም ብሩህ አዕምሮ ያላት፣ ከፍተኛ የትምህርት ውጤት የነበራት አንዲት ልጃገረድ፣ አንዳንድ ወንዶች በዕውቀት የሚበልጧቸውን ሴቶች ለጋብቻ መጠየቅ እንደሚፈሩ ስላወቀች፣ ወንዶችን ለመሳብ እንድትችል ራሷን ምኝና ማሰብ የማትችል አድርጋ ለማሳየት ሞከረች። ይሄም ሆኖ ተሳክቶላት

[4] William L. Blevins. Care and Maintenance for Christian Life, Word Books Publisher. Waco, TX.

የሚያገባትን ወንድ አላገኘችም። መጠኑና ዓይነት የተለያየ ይሁን እንጂ፣ ከላይ እንደገለጽናት ሴት የራሳቸው የሆነ አስመሳይነት ያላቸው ብዙዎች ናቸው። አይወቁት እንጂ በመንፈሳዊ ሕይወትም ከዚህ የተለየ አይደለም። ሁለት ዓይነት ሕይወት ስለሚኖሩ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ሥፍራ በግልጽ ይናገራል፥

> *"እግዚአብሔርን እወድዳለሁ እያለ ወንድሙን የሚጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድድ ከሆነ፣ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወድድ አይችልም" (1 ዮሐ. 4:20)።*

> *"ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት አለን" እያልን በጨለማ የምንኖር ከሆንን እንዋሻለን፤ በቃላችንም ሆነ በሥራችን እውነት የለም ማለት ነው" (1 ዮሐ. 1:6)።*

> *ስለሌሎች ግድ የሌለን ሆነን፣ "እምነት አለን" እንላለን (ያዕ. 2:4-16)።*

> *የእግዚአብሔርን ፈቃድ ችላ ብለን እየኖርን "ኢየሱስ ጌታ ነው" እንላለን (ማቴ. 7:21)።*

ከላይ እንዳየነው ሁለት ዓይነት አቋም ወይም መልክ ያላቸው አማኞች፣ እውነተኛውን ማንነታቸውን ለመሰወር ራሳቸውን የሚደብቁ፣ ያልሆኑትን መስለው ለመታየት የሚሞክሩትን መጽሐፍ ቅዱስ "ግብዝ" ብሎ ይጠራቸዋል። እግዚአብሔር ሰውን ግሩምና ድንቅ አድርጎ የሠራው መሆኑን እያወቁ፣ አንዳንድ ሰዎች ልክ እግዚአብሔር እንደፈጠራቸው ራሳቸውን መሆን የሚያቅታቸው፣ ወይም ራሳቸውን ለመለወጥ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉት ለምን ይሆን? ወደዚህ ዓለም የመጡት በድንገት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ፣ የእርሱን ዓላማና ፈቃድ ለመፈጸም ከሆነ፣ እነርሱ የተመደቡበትን ሥራ ከእነርሱ በስተቀር ሌላ ማንም ሰው ጥሩ አድርጎ ሊሠራው የማይችለው መሆኑን እያወቁ፣ እግዚአብሔር ያቀደላቸውን ዓላማ ለመፈጸም፣ ራሳቸውን ሆነው በመቅረብ ፋንታ ሌላውን ለመሆን የሚሞክሩት ለምን ይሆን?





በሰብአዊነታችን ሁላችንም የምንመሳሰልበት ነገር እንዳለ ከላይ ገልጸናል። ዓላማውን ለመፈጸም የሚያስችለንን አቅም ለሁላችንም ከፈጣሪያችን የተሰጠን የተፈጥሮ ችሎታ አለን። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ የበላይ የሚያደርገን የተፈጥሮ ባሕርያት ከእግዚአብሔር ተሰጥቶናል። ይኸውም የማሰብ፣ የማመዛዘን ስጦታ፣ ለምንጠየቀው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ተሰጥቶናል። ሁላችንም የመፍቀድና የመምረጥ ችሎታ አለን። በእነዚህ ነገሮች የሰው ልጆች ሁሉ ተመሳሳይነት አለን። በሌላ በኩል ደግሞ አንዱ ከሌላው ፍጹም የተለየ የሚያደርገው የራሱ የሆነ መለያ አለው።

እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ከጨረሰ በኋላ፣ የፈጠረው ሁሉ እንከን የሌለበት መሆኑን አይቶ *"ሁሉም መልካም ነው"* አለ (ዘፍ. 1:25)። ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሲወጣና ኃጢአት ወደ ሕይወቱ ሲገባ ፍጹምነቱን ይጣ እንጂ፣ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ግሩምና ድንቅ አድርጎ ነው። ዘማሪው ስለዚህ እውነት ሲመሰክር፣ ***"ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ"*** ይላል *(መዝ. 139:14)*። እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ከፈጸመ በኋላ *"መልካም ነው"* ሲል፣ በምድር ላይ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ብቻ ሳይሆን፣ ሰውንም ይጨምራል። ይህ እውነት ከሆነ፣ ታዲያ ሰው እግዚአብሔር *"መልካም ነው"* ያለውን፣ መልካም እንዳልሆነ አድርጎ በመቁጠር ራሱን ልክ እንዳለ በመቀበል ፈንታ ማንነቱን ለመለወጥ ሙከራ የሚያደርገው ለምን ይሆን?

ሰው የችግሩ ዋና ምክንያት ሌላው ሰው ሳይሆን እርሱ ራሱ ነው። ያለማቋረጥ የሚጨቀጭቀው፣ ከውስጡ የሚወጣው ድምጽ አለ። ያም ድምጽ፣

- *"አትረባም! ትልቅ አይደለህም! ተልቀህ ለመታየት እንደ እከሌ ሁን፤ እርሱ የሚያደርገውን አድርግ፤ ሰፊውን ሕዝብ መስለህ ኑር" የሚለው ነው።*

እግዚአብሔር ልዩ አድርጎ እንደ ፈጠረው ቢያውቅም፣ ሌላውን እንዲመስል ወይም እንዲሆን ያባብለዋል። ብዙዎች ያልተረዱት እውነት

ቢኖር፣ ምንም ያህል ቢሞክሩ ሌላውን መሆን የማይችሉ መሆናቸውን ነው። እያንዳንዱ ሰው የተፈጠረው የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወቱ ለመፈጸም ነው። ሌላውን ሰው ለመሆን ሲሞክር፣ እርሱ የተፈጠረበትን ዓላማ መሳቱ እንደሆነ፣ በአገልግሎቱ ውጤት *"አንደኛ"* በመሆን ፈንታ *"ሁለተኛ"* መሆንን መምረጡ እንደሆነ የሚረዳው አይመስለንም። ምክንያቱም እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ሲፈጥረን፣ የተፈጠርንበትን ዓላማ ለመፈጸም ከማንኛውም ሰው የበለጠ ችሎታ፣ ኀቅም የሰጠው ለእኛ ስለሆነ ነው።

## *5. እምነታችን በሌላው ሰው ልምምድ ላይ የተመሠረተ ይሆን?*

የማንኛውም ሰው የክርስትና ሕይወት የተመሠረተው በሌሎች ሰዎች የሕይወት ልምምድና እምነት ላይ ሳይሆን፣ በራሱ የግል ልምምድ ላይ መሆን አለበት። ሰው በግሉ ከጌታ ጋር ትክክል የሆነ ግንኙነት መፍጠር አለበት። ካርቦን ኮፒ የሆነ ክርስትና የለም። በመንፈሳዊ ሕይወት ራሳችንን በመሆን ፈንታ ሌላውን ሰው ለመምሰል መሞከር ጎጂ እንጂ ጥቅም የለውም። በክርስቲያኖች መካከል ትልቁ ችግር ወይም አሳዛኝ የሆነው ነገር አንዳንድ ክርስቲያኖች ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌሎችን ለመሆን ጥረት ሲያደርጉ መታየታቸው ነው።

ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም ሲቀርብ፣ አስደንጋጭ የሆነ የወታደር መልክ ስላልነበረው፣ የዳዊትን መልክ ለመለወጥ ሳኦል የራሱን ዕቃ ጦር አለበሰው። ይሁን እንጂ፤ የሳኦል ልብስና ዕቃ ጦር ልኩ ስላልሆነና ስላልተመቸው፣ ያንን አውልቆ የአባቱን በግ ሲጠብቅ የሚለብሰውን የራሱን ልብስ ለበሰ። ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም ሲቀርብ፣ ወታደር ሆኖ ሳይሆን በግ ጠባቂ ሆኖ ነው። ሳዖል የሞከረው ዳዊትን ወታደር ሳይሆን ወታደር እንዲመስል ነበር።

ዛሬ በየቦታው የምናየው ችግር ወይም ሁከት ቢኖር አንዳንዶች ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌላውን ሰው ለመሆን መሞከራቸው ነው። ራሳ





ችንን መሆን ትተን ሌላ ሰው ለመሆን ስንሞክር እግዚአብሔርን "ስት ሠራኝ ትክክል አድርገኸ አልሠራኸኝም" ማለታችን እንደሆነ የተረዳነው አይመስለንም። እግዚአብሔር ከተጠቀመባቸው ታላላቅ ሰዎች ምክርና ሀሳብ መቀበል፣ ሚዛኑን ያልለቀቀ አድናቆት መስጠት ስሁተት የለበትም። የእነርሱ ፎቶ-ኮፒ መሆን ግን ለራሳችን ዕድገት መከልከላችን ይሆናል። አሜሪካን አገር ውስጥ ከብዙ ዓመት በፊት የሞተውን *"ኤልቪስ ፕሬዝሊን"* ለመምሰል ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉ ብዙዎች አሉ፣ በእኛ አገር ያሉ አንዳንድ ወጣት ሰባኪዎች *"ዋቤኒ ሂንና የናይጄሪያዊው ጆሹዋ"* ካርበን-ኮፒ ወይም ግልባጭ ለመሆን የሚሞክሩ አሉ። እነዚህ ሊኮርጁዋቸው የሚጥሩትን ሰዎች እውነተኛውን ማንነታቸውን፣ የተደበቀ ሕይወታቸውን በደንብ ቢያውቁ፣ እንኳን እነርሱን ለመምሰል ቀርቶ፣ አጠገባቸው መቅረብ፣ ስለ እነርሱ መስማትም አይፈልጉም ነበር።

እግዚአብሔር ከማይወዳቸው ነገሮች መካከል አንደኛው፣ ራሳችንን በመሆን ፈንታ ሌላውን ሰው ለመሆን የምናደርገውን ሙከራ ነው። ሌላውን ኮፒ ማድረግ ውጪያችንን እንጂ ውስጣችንን አይለውጥም። ውስጣችን ካልተለወጠ ደግሞ ለውጣችን እውነተኛ ለውጥ አይደለም። ብዙ ጊዜ ችግር ውስጥ የሚከተን፣ ውስጣችንና ውጪያችን አንድ ዓይነት ባለመሆኑ ነው። *"ግብዝነት"* የሚያሰኘን ይኸው ነው። ውስጡና ውጪው አንድ ዓይነት ያልሆነውን ሕይወታችንን ልንሸፍነው ብንሞክርም እንኳን ጉራማይሌ ሆኖ መታየቱ አይቀርም። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መኮረጅ እንችላለን፤ እውነተኛ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬን መኮረጅ ወይም ኮፒ ማድረግ ግን አንችልም። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንዳለን ለተወሰነ ጊዜ ማስመሰል እንችላለን። ይሁን እንጂ ስደት፣ መከራ፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ፈተናና ችግር ሲደርስብን ወዲያው እውነተኞች እንዳልሆንን ይታወቃል።

## 6. ራሳችንን ለመሆን ነጻነት አለን፥

ሕጻን ልጅ ቢጣፍጠውም ባይጣፍጠውም፣ ወላጆቹ አፉ ውስጥ ያደረጉትን ሁሉ መብላት አለበት። እንኳሉ እንደሚገባው ገና ያልዳበረ በመሆኑ፣ የራሱን ምርጫ ማድረግ ስለማይችል፣ ወላጆቹ ሊመርጡለት ይገባል። እያደገ ሲመጣ ግን የማይፈልገውን ዓይነት ምግብ ሲሰጡት፣ ከሚችለው በላይ ሲያጎርሱት፣ ያጎረሱትን መትፋት፣ እንዲሁም "ከዚህ በኋላ አልበላም ወይም አልጠጣም" ለማለት አፉን ጥርቅም አድርጎ የሚዘጋበት ጊዜ አለ። የአሁኑን አላውቅም፣ እኛ ልጆች በነበርንበት ዘመን የአገራችን ወላጆች ልጆች ጡጦ አልጠባም ሲሉ፣ ልጆቻቸውን በግድ የሚግቱበት ጊዜ ነበር። ይሄም ሆኖ መጋት የማይፈልጉ አንዳንድ ሕጻናት አፋቸውን ጥርቅም አድርገው ይዘጉ ነበር። ለመጋት አስቸጋሪ የሆኑ ልጆች ያሏቸው አንዳንድ ወላጆች ያገኙት ብልሃት፣ በአፍንጫቸው እንዳ ይተነፍሱ የልጆቻቸውን አፍንጫ መያዝ ነው። አፋቸውና አፍንጫቸው ከተዘጋ መተንፈስ ስለማይችሉ፣ ከሁለት አንዱን የግድ መክፈት አለባቸው። አፍንጫቸው በእናታቸው ቁጥጥር ሥር የዋለ ስለሆነ፤ በህጻን ጉልበታቸው ማሸነፍ ስለማይችሉ በራሳቸው ፈቃድ የዘጉትን አፋቸውን በግድ ይከፍታሉ። ለመተንፈስ ሲሉ፣ አፋቸውን ሲከፍቱ እንዲጠጡ የቀረባቸውን ወተትም ሆነ ሌላ ፈሳሽ ነገር ወደ ውስጥ መግባት ይጀምራሉ።

የራሳቸው የሆነ ብርቱ ፈቃድ ያላቸው አንዳንድ ሕጻናት፣ "የማልፈልገውን በግድ አታበሉኝም፥ ይህንን ከምበላ ወይም ከምጠጣ ብሞት ይሻለኛል" የሚሉ ይመስላል። አፋቸውን በመክፈት ፈንታ ከተያዙበት ፈልቅቀው ለመውጣት ባላቸው ኃይል ሁሉ ይፈራገጣሉ። ልጆች ከመጋት ዕድሜ ሲያልፉ፣ ሀሳባቸውን በንግግር መግለጽ ሲችሉ፣ የማይፈልጉት ምግብ ሲሰጣቸው፣ ከሚችሉት በላይ "ብሉ" ሲባሉ "ጠግቤአለሁ! በቃኝ!" ማለት ይጀምራሉ። ሁላችንም በዚህ ዓይነት ልምምድ ውስጥ አልፈን ነው ዛሬ በተራችን ወላጆች ሆነን፤ እኛ እንደተጋትነው ባንግታቸውም ልጆቻችን የሚጠቅማቸውን ዓይነት ምግብ እንዲበሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ዘዴና ብልሀት ፈጥረን እንዲበሉ የምናደርጋቸው።





የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገታችንስ ምን ዓይነት ይመስል ይሆን? ከእስላም ቤተሰብ ከሆንን እስላሞች፣ ከክርስቲያን ቤተሰብ ከሆንን ክርስቲያኖች እንሆናለን። እርግጥ ነው ልጆች ሆነን፣ በወላጆቻችን ሥር በምንኖርበት ወቅት የመምርረጥ መብት ስለሌለን የሚያምኑትን እናምናለን፥ የሚቀበሉትን እንቀበላለን። አድገን ራሳችንን ስናውቅ፣ ክፉውንና ደጉን መምረጥ ስንችል ግን፣ የራሳችን የሆነ እምነት፣ የራሳችን የሆነ አቋም ሊኖረን ይገባል። ጨሌ በሚያመልኩ፣ ለውቃቢ ቡና እያፈሉ ከሚኖሩ ቤተሰብ ውስጥ ካደግን፣ "ወላጆቼ የተቀበሉት ስለሆነ እኔም መቀበል አለብኝ" የሚል አቋም ብንይዝ፣ እግዚአብሔር የሰጠንን አዕምሮ እንደሚገባው ያልተጠቀምንበት መሆናችንን ያሳያል። ካደግን በኋላ መርጠን፣ አመዛዝነን፣ እውነቱን መርምረንና ፈትነን መልካም የሆነውን እንድንቀበል ውሳኔው የራሳችን ነው። "የሆኑትን እንሆናለን፥ የተቀበሉትን እንቀበላለን፥ ያመኑትን እናምናለን" የሚሉ አሉ። ይሄም ትክክል የሆነ አባባል አይመስለንም።

አንዳንድ ሰዎች በግላቸው መርጠው የሚስማማቸውን በመከተል ፈንታ በመኩራራት ወይም በሙሉ ልብ "የእናትና አባቴን ሃይማኖት እከተላለሁ" ሲሉ መስማት ለብዙዎቻችን አዲስ አይደለም። ሀብትና ንብረት ከወላጆቻችን እንደምንወርሰው ሃይማኖትም ይወረስ ይሆን? በእምነት የራሳችን አቋም ሳይኖረን የወላጆቻችን ፎቶ ኮፒ በመሆን ብቻ መንግሥተ ሰማይ ያስገባን ይሆን? እግዚአብሔር ልጆች እንጂ የልጅ ልጆች የሉትም። እግዚአብሔር አባት እንጂ አያት አይደለም። ደህንነት ከቤተሰብ የሚወረስ ቢሆን ኖሮ፣ የክርስትና ሕይወት በጣም ቀላል ይሆን ነበር። ነገር ግን ሁሉም የራሱን ምርጫ ማድረግ አለበት። በራሱ እምነት እንጂ፣ በወላጆቹ እምነት አይድንም። በወላጆች እምነት የሚዳን ቢሆን ኖሮ ብዙ ወንጀለኞችና ነፍሰ ገዳዮች መንግሥተ ሰማይን ያጣብቡት ነበር።

አዕምሯችን እየዳበረ ሲመጣ መንፈሳዊ ደህንነት ከወላጆች በሚወረስ ሃይማኖት ወይም እምነት እንደማይገኝ መረዳት ስንችል፤ ወላጆቻችን ከተቀበሉትና ካመኑት ሃይማኖት ውጪ እውነተኛውን መፈለግ እንጀምራለን። ወላጆቻችን የሚኖሩት መንፈሳዊ ሕይወት ሳይጣፍጠን ይቀርና

"እምቢ" ማለታችን አይቀርም። የሚያሳዝነው አንዳንድ ወላጆች ሕጻን ልጆቻቸውን ወተት እንደሚግቱ የራሳቸውን ሃይማኖት በኃይል ልጆቻቸውን መጋት የሚፈልጉ አሉ። "እምቢ" ካሉ፤ "የእናት አባትህን ሃይማኖት ትተሃልና እከድሃለሁ… የውርስ ተካፋይ አትሆንም፥.. ከቤቴ ውጣልኝ… ዓይንህን ማየት አልፈልግም.." የሚሉ ወላጆች አሉ።

በዚህ ምክንያት ወላጆቻቸውን የፈሩ፣ ከእውነተኛው መንፈሳዊ ሕይወት ሸሽተው የሚኖሩ እንዳሉ የታወቀ ነው። በዚህ ዓይነት ልጆቻቸው በራሳቸው አዕምሮ እንዳያስቡ፣ "እኛ እናስብልሀ"፣ የራሳቸውን ምርጫ እንዳይመርጡ 'እኛ እንምረጥልሀ" ራሳቸው አኝከው እንዳይውጡ፣ "እኛ አኝከን እናጉርስህ፣ ወይም አፍህ ውስጥ እንትፋልህ" የሚሉ ሰዎች አሉ። በዚህ ዓይነት ልምምድ ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች፣

*ሁልጊዜ የራሳቸው የሆነ አቋም፣ የራሳቸው የሆነ እምነትና መመሪያ የሌላቸው ይሆናሉ።*

*ወደነፈሰበት የሚነፍሱ ይሆናሉ።*

*ሁልጊዜ ሕይወታቸውን የሚመሩት ከሌሎች በቀዱት ወይም በኮረጁት ሀሳብ ላይ ነው።*

*የራሳቸው የሆነ ነጻ አስተሳሰብ፣ ምርጫና እምነት የላቸውም።*

*ሁልጊዜ ሕይወታቸውን የሚመሩት ከሌሎች እየቀዱ ወይም እየኮረጁ ነው።*

የክርስትና ሕይወት አቋም የለሽ፣ ካርቦን ኮፒ የሚደረግ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው በግሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲነካው፣ ኃጢአቱ እንዲታየው ብቻ ሳይሆን፣ በግሉ ንስሀ ገብቶ ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ መቀበል አለበት። ዋጋ እንደሚያስከፍለው አውቆ የራሱን ውሳኔ መወሰን አለበት።





## *7. ካርቦን-ኮፒ መሆን አስተዳደጋችን ያመጣው ተጽዕኖ ይሆን?*

የሰውን ባሕሪ ለመቅረጽ አስተዳደጉ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ልጆች ከወላጆቻቸው፣ ከአስተማሪዎቻቸው፣ ከቅርብ ጓደኞቻቸው፣ ከወንድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው ስለራሳቸው እየሰሙ ያደጉት አሉታዊ አስተያየት ይኸውም፣ "አትረባም፣ እንደ ወንድምህ ጎበዝ አይደለህም" የሚል ከሆነ፣ ሁልጊዜ ራሳቸውን የሚመለከቱት ዝቅ አድርገው ነው። በተለይ ሰዎች "ነህ!" ያሏቸውን አምነው ከተቀበሉ፣ ሌሎች ከደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ የሚያስችል አቅምና ችሎታ ያላቸው መስሎ አይሰማቸውም። ደካማነታቸውንና ተሸናፊነታቸውን እንጂ ብርታታቸውን ማየት አይሆንላቸውም። በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጡ፣ ለጠላቶቻቸው ቶሎ እጅ የሚሰጡ ይሆናሉ። ይሄም በራሳቸው እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋቸዋል።

*ዶክተር ኬቨን ሌመን "When Your Best Is Not Good Enough"* በሚለው፣ ሰፊና ጥሩ ትምህርት በያዘው መጽሐፋቸው ስለ ሕይወት ጉዟቸው በመጠኑ ጠቅሰዋል። በልጅነታቸው በትምህርታቸው ደካማ በመሆናቸው፣ *"ወደፊት ከትልቅነት ደረጃ ይደርሳል"* ብሎ እምነት የጣለባቸው ሰው አልነበረም። ስለ ቀደመው ሕይወታቸው ሲጽፉ፣

> *"የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን የጨረስኩት በከፍተኛ ውጤት ሳይሆን፣ የክፍሉ መጨረሻ ሆኜ ነው። የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ብዙ የአስተማሪዎቼን ልዩ ድጋፍ እያገኘሁ ነው የጨረስኩት። ኮሌጅ ገብቼ ትምህርቴን ሳልጨርስ ወጣሁ። ለተወሰነ ጊዜ አንድ ሆስፒታል ውስጥ የጽዳት ሠራተኛ ሆኜ ስሠራ፣ የነርሶች ኃላፊ የነበረችው ሴት፣ ከእኒ ጋር የቅርብ ጓደኝነት የጀመረችውን ሴት አንድ ቀን ለብቻዋ ወስዳ፣ 'ከዚህ ሰው ጋር ለምን ጊዜሽን ታባክኛለሽ? ይሄ ሰው ወደ ፊት የትም መድረስ ስለማይችል አይረባሽም' አለቻት። ጓደኛዬ ግን ምክሯን አልተቀበለችትም። ምክሯን አትቀበላት እንጂ፣ በዚያን ወቅት የነርሶች ኃላፊዋ ለጓደኛዬ የሰጠቻት ምክር መስዬ የታየኋትን ነበር። በወቅቱ እኔ ስለ ራሴ ከነበረኝ እምነት የበለጠ እጮኛዬ*

*በእኔ ላይ እምነት ነበራት" አሉ።*[5] መጠነኛም ይሁን እንጂ፣ በራሳቸው እምነት ስለነበራቸው፣ መድረስ ከሚገባቸውው ደረጃ ላይ መድረስ ቻሉ።

ከላይ ያነበብነው *የዶክተር ኬቨን ሌመን* እውነተኛ ታሪክ ለብዙዎች ጥሩ ትምህርት የሚሰጥ ነው። *ዶክተር ኬቨን ሌመን* ከየት ተነስተው የት እንደደረሱ ለመረዳት ይህን ያህል ከባድ አይደለም። ሰዎች *"አይረባም! ተስፋ የለውም"* እንዳሏቸው፣ አባባላቸውን ተቀብለው *"እውነትም ተስፋ የለኝም! አልረባም"* ብለው እጃቸውን አጣምረው ቢቀመጡ ኖሮ፣ ዛሬ መጽሐፋቸውን ያነበቡ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሰፊ ትምህርት ከእርሳቸው ማግኘት ባልቻሉም ነበር። ሌሎች ባያምኑባቸውም፣ "አይረባም" ቢሏቸውም፣ እርሳቸው ግን በራሳቸው አምነው መድረስ ከሚችሉበት ደረጃ መድረስ ቻሉ። በራሳቸው እምነት በማጣት ምክንያት ብዙዎች ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌላውን ሰው ለመሆን የሚሞክሩበት አንደኛው ምክንያት ይሄው ነው።

አስተዳደጋችን፣ ወይም የባህል ተጽኖ ኖሮብን ይሆን ብዙዎቻችን ጠንካራ የሆነ የራሳችን የሆነ አቋም ይዘን ለረጅም ጊዜ በምናምነው ነገር ጸንተን መቆም የማንችለው? የማናምንበትም እንኳን ቢሆን ሌሎች ስለተቀበሉትና ስላደረጉት ብቻ የምንቀበለውና የምናደርገው ለምን ይሆን? በራሳችን አዕምሮ አመዛዝነን፣ መርጠን፣ መርምረንና ፈትነን የሚበጀንን በማድረግ ፈንታ ሌላውን ኮፒ ማድረግ ከተፈጥሮ ባህሪያችን እንደ አንዱ የሆነው አስተዳደጋችን ፈሪዎች እንድንሆን፣ አዲስ ነገር፣ ያልተፈተነ ነገር በግላችን እርምጃ እንዳንወስድ አድርጎን ይሆን?

ይህን ዓይነት ባሕሪ ሥጋዊ ሕይወታችንን ከሚጎዳው የበለጠ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ይጎዳዋል። በሰለጠነው ዓለም አንዱ የፈለሰፈውን ሌላው ቀድቶ እንዳይጠቀምበት የሚከለክል ሕግ አለ። መጀመሪያ የፈለሰፈው ሰው፣ ሌላ ሰው ኮፒ እንዳያደርገው፣ የተፈለሰፉትን ነገሮች የሚመዘግብ መሥሪያ ቤት አለ። መሥሪያ ቤቱ፣ ለፈለሰፈው ሰው

---

[5] Kevin Leman. When Your Best Is Not Good Enough. Fleming H. Revel, Grand Rapid, MI, 1988.





"የፈጠራ ሥራ ባለቤትነት ማረጋገጫ" (Patent Right) መብት ይሰጠዋል። የዚህም ዋና ዓላማ የሌላውን ሥራ ኮፒ አድርገው ለመጠቀም የሚሞክሩትን ሰዎች ለመግታት የታሰበ ነው።

የክርስትና ሕይወት *"ካርቦን-ኮፒ"* መሆን የማይፈቀድበት ቢሆንም፣ የዚህ ችግር ያለባቸው ሰዎች ጥቂቶች እንዳልሆኑ እናውቃለን። የመጣውን ሁሉ ይቀበላሉ። አንዱ ያደረገውን፣ ሌላውም ያደርጋል። የማይታመንም እንኳን ቢሆን፤

*አንዱ ካመነ፣ እነርሱም ያምናሉ፣*

*አንዱ ቢጸልይ ካለቀሰ፣ ማልቀስ ደንብ ይመስላቸውና የሚያለቅሱ አሉ፣*

*አንዱ ከሳቀ፣ እነርሱም ይስቃሉ (በመንፈስ መንከትከት)*

*አንዱ መሬት ላይ ከተዘረረ፣ ወይም ከተንከባለለ፣*
*እነርሱም ይንከባለላሉ (በመንፈስ መዘረር)፣*

የሚያደርጉትን ነገር አምነውበት፣ ጠቃሚ መሆኑን መርምረውት ሳይሆን፣ ሌሎች ስላደረጉት ብቻ የሚያደርጉ ብዙዎች አሉ። የሌላው ሰው ፎቶ-ኮፒ መሆናቸው እንደሆነ ልብ ያሉት አይመስለንም። በዘመናችን ሳይታወቅ ከክርስትና እምነት ጋር ተቀላቅለው በመግባታቸው ምክንያት እንደ ሃይማኖት ክፍላችን የተቀበልናቸው ብዙ ዓይነት ልምምዶች አሉ። እንግዳ የሆኑ ልምምዶች በቤተ ክርስቲያናችን ሊበዙ የቻሉት፣ ሌላውን ዝም ብለው ኮፒ የሚያደርጉ ክርስቲያኖች ስለ በዙ ነው።

እግዚአብሔር ማሰብ እንድንችል፣ የራሳችንን ምርጫ እንድንመርጥ ጥሩ አዕምሮ ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ በአዕምሮ መጠቀም ኃጢአት ስለሚመስለን እንደሚገባው አንጠቀምበትም። ጥሩ አዕምሮ፣ ሰፊ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች እንዳይመሩን፣ እንዳያስጠነቅቁን፣ እንዳይመክሩን ከመካከላችን በተለያየ መንገድና ዘዴ ገፍተን አስወጥተናቸዋል። ሌላውን ኮፒ ማድረግ ካለመብሰል የሚመጣ ነው። ሕጻናት ልጆቻችን፣ ወንዶች የአባታቸውን፣ ሴቶች የእናታቸውን ጫማ አድርገው "እንደ አባባ...

እንደ እማማ" በማለት ለመራመድ ሲሞክሩ አይተንል። በሥጋም፣ በአምሮም ካደጉ በኋላ ግን አባታቸውንም ሆነ እናታቸውን የመከረጅ ፈተና የለባቸውም። በመንፈሳዊው ዓለም ግን ሁልጊዜ የማያድጉ፣ የሌላው ሰው ግልባጭ፣ ወይም ካርቦን-ኮፒ ሆነው የሚቀሩ አማኞች ብዙዎች ናቸው።

## *8. እግዚአብሔር ራሳችንን ለመሆን ነጻነት ሰጥቶናል፥*

ያልገባኝን ለመጠየቅ፣ በደንብ ያልተረዳሁትን ለመመርመር እግዚአብሔር ነጻነት እንዳልከለከለኝ አምናለሁ። ሳይገባኝ፣ ውስጤን ሳይነካው፣ *"እከሌ ተቀብሎታልና ዝም ብለህ ተቀበል፥ እርሱን ኮፒ እያደረግህ ሕይወትህን ምራ። አገልግሎትህ የእከሌን ዓይነት ይሁን"* አይለኝም። እኔ ከማምነው እምነት ውጪ የሚያምኑ ብዙዎች ስላሉ፣ ብዛታቸውን ብቻ አይቼ እነርሱን ኮፒ ማድረግ፣ ወይም እነርሱን መምሰል አልፈልግም። ብዛት የአንድ ነገር እውነተኛነት ወይም ትክክለኛነት መመዘኛ ወይም መለኪያ አይደለም። ለምሳሌ፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ቁጥራቸው ብዙ ነው። ይሁን እንጂ፣ እምነታቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያስገባ ነው ማለት አይደለም። ጥቂቶችም ብንሆን፣ ወይም ብቻችንንም ብንቀር፣ ላመንበት ነገር እስከ ሞት ድረስ ቆራጦች መሆን ያስፈልገናል።

ይህን ዓይነት አቋም ካለን፣ ሌላውን ኮፒ እያደረግን ወይም እየመሰልን መኖር ያቅተናል። ባቢሎን ውስጥ ሕዝቡ ሁሉ *ናቡከደናጾር* ላቆመው ምስል ሲሰግድ *ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ* ግን *"ለጣኦቱ እንሰግድም"* በማለት ብቻቸውን መቆም እንዳላስፈራቸው እናስታውሳለን። እነዚያ ሦስት ዕብራውያን ከሰፊው ሕዝብ ተለይተው *"ለጣዖቱ አንሰግድም"* ሲሉ፣ እምቢተኛነታቸው አደጋ እንደሚያስከትልባቸው ያውቁ ነበር። ዛሬ ብዙዎች ከሚነፍሰው ጋር የሚነፍሱት ራሳቸውን ከአደጋ ለማዳን ሳይሆን፣ የራሳቸው የሆነ አቋም የሌላቸው በመሆናቸው ብቻ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ *"ከሚነፍሰው ጋር አልነፍስም፣ ሌሎች ስላመኑ ብቻ አምናለሁ"* ያላለ፣ ደፋር፣ ብዙዎች *"በደካማነት፣ በተጠራ





ጣሪነት"* የሚያውቁት ቶማስ አንደኛው ነው። *"ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል፤ አይተነዋል"* ያሉትን ደቀ መዛሙርቱን፤

- *"በምስማር የተወጉትን እጆቹን ካላየሁን ጣቴን ካላገባሁ፣ እጄንም በጎኑ ቁስል ካላገባሁ አላምንም አላቸው" (ዮሐ. 20፡25)።*

### *8-ሀ ቶማስ የአቋም ሰው ነበር፥*

አዲስ ኪዳን ውስጥ *"ካርቦን ኮፒ አልሆንም፥ የራሴ የሆነ የግል አቋም አለኝ፥ ሌሎች ስላመኑ ብቻ ማመን አልፈልግም"* በማለት ለብቻው ጸንቶ የቆመ ሰው ቢኖር *ቶማስ* አንደኛው ነው። ስለ ሌሎች ደቀ መዛሙርት የምናውቀውን ያህል ስለ ቶማስ ብዙ አናውቅም። ቶማስ በተፈጥሮው ፊት ለፊት የሚናገር፣ ቀጥተኛ፣ የሚያስበውንና የሚያምንበትን ለመናገር ወደ ኋላ የማይል፣ እውነተኛ፣ ፍጹም ግብዝነት የሌለበት፣ የራሱ የሆነ አቋም ያለው፣ እጅግ በጣም የሚደነቅ ባሕሪ ያለው ሰው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ *"ቶማስ ዲዲሞስ"* ብሎ ይጠራዋል። የስሙ ትርጉም *"መንታ"* ማለት ነው። *"መንታ"* የሚለው ቃል ምናልባት የቅጽል ስሙ ሳይሆን አይቀርም የሚሉ የሥነ መለኮት ምሁራን አሉ። እኛም *"ተጠራጣሪው ቶማስ"* የሚል የቅጽል ስም ሰጥተነዋል። ይህንን ስም የሰጠነው በማድነቅ ሳይሆን፤ አሳንሰን በማየት ነው።

*ቶማስን "ተጠራጣሪው"* ከምንለው ይልቅ፣ *"የሚሰማውን ከልቡ የሚናገር፣ እውነተኛና ሀቀኛው ሰው"* ብንለው የሚበዛበት አይሆንም ነበር። የቶማስን እውነተኛነትና ሀቀኝነት ከሚያደንቁ ሰዎች መካከል አንደኛው ዮሐንስ ነው። ዮሐንስ በጻፈው ወንጌል ላይ ቶማስን አራት ጊዜ ያህል ጠቅሶት እናያለን። እነዚህም አራት ጊዜያት በጣም አሳሳቢና ቀውጢ ወይም ጠባብ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ በነበረበት ጊዜ ነው።

(1) *የመጀመሪያው፣* ኢየሱስ በምድር የተመደበለትን አገልግሎት ሊጨርስ ትንሽ በቀረው ወቅት፣ የሃይማኖት መሪዎችና ባለሥልጣናት በኢየሱስ ላይ ከምንጊዜውም የበለጠ ግፊት ባበዙበት፣ ሊገድሉት በሚፈልጉበት፣ ተከታዮቹ የነበሩት አብዛኛዎቹ ወደ ኋላ ባፈገፈጉበት ወቅት ነው። ኢየሱስን ይዘው በድንጋይ ሊወግሩት በሚሞክሩበት ቀውጢ

በሆነችበት ሰዓት፣ ክርስቶስና ተከታዮቹ ከሞት ለጥቂት ድነው ከማያስጋቸው ሥፍራ ከሆኑ በኋላ ነው።

በዚህ ወቅት የኢየሱስ ወዳጅ የነበረው አልአዛር በጣም ታሞ ነበር። ኢየሱስ አልአዛርን ለመፈወስ "ልሂድ" እንደሚል፣ ከሄደ ደግሞ ጠላቶቹ ይዘው እንደሚገድሉት፣ ደቀ መዛሙርቱም ለአደጋ እንደሚጋለጡ በመገንዘብ "እንሂድ" ቢላቸው ከክርስቶስ ጋር አብሮ ለመሄድ ፈቃደኞች እንደማይሆኑ ግልጽ ነበር። የፈሩት አልቀረም፤ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን *"ወደ ይሁዳ ክፍለ ሀገር እንደገና እንሂድ አላቸው"* (የዮሐ. 11፥7)። ደቀ መዛሙርቱም ሁኔታው ስላስፈራቸው *"መምህር ሆይ! አይሁዳውያን ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር፥ ታዲያ እንደገና ወደዚያ ተመልሰህ ትሄዳለህ? አሉት"* (የዮሐ. 11፥8)። ኢየሱስም በፍርሃት የተሞላውን የደቀ መዛሙርቱን ልብ ለማረጋጋት ቢሞክርም አብረውት ለመሄድ ፈቃደኞች አልነበሩም። ኢየሱስ የአልአዛርን መሞት ሲገልጽላቸው፣ *"ወዳጃችን አልአዛር አንቀላፍቷል፥ እኔ ግን ከእንቅልፉ ላስነሳው እሄዳለሁ አላቸው"* (የዮሐ. 11፥11)። ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ የተናገረው ንግግር በደንብ ስላልገባቸው፣ *"ጌታ ሆይ! አንቀላፍቶ ከሆነ ተሽሎታል ማለት ነው አሉት" (የዮሐ. 11፥12)።*

ኢየሱስ ለመሄድ እንደቆረጠ ሲያውቁ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ በፍርሃት ተሞልተው ወደ ኋላ ሊያፈገፍጉ ሲያስቡ፣ ጉዟችን አደጋ ቢያስከትልብንም ኢየሱስን ተከትለን መሄድ አለብን ያለው ቶማስ ብቻ ነበር።

➢ *"በዚህ ጊዜ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት 'ከእርሱ ጋር እንድንሞት እኛም እንሂድ' አላቸው"* (የዮሐ. 11፥16)።

*ፀ-ለ ቶማስ ልበ ቆራጥ ሰው ነበር፥*

እዚህ ላይ የቶማስ ልበ ቆራጥነት፣ ለሚያምንበት ነገር ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ሰው መሆኑን ያሳየናል። "ኢየሱስ የሚሞት ከሆነ ብቻውን መሞት ስለሌለበት አብረነው መሞት አለብን" ማለቱ ነበር። ድፍረቱና ታማኝነቱ የሚያስከትልበት አደጋ ከፍተኛ መሆኑን ቢያውቅም፤ ቶማስ





አስፈላጊውን ዋጋ ለመክፈል የተሰጠ ሰው ነበር። ለክርስቶስ የነበረው ፍቅርና አክብሮት፣ የክርስቶስ ሕይወትና የሚያስተምረው ትምህርት ምን ዓይነት ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው በትክክል የተረዳ ሰው ነበር። ከክርስቶስ ውጭ ሆኖ በሕይወት ከመኖር ይልቅ፣ ከክርስቶስ ጋር ሆኖ መሞትን የመረጠ ቆራጥ፣ ሙሉ ልብ ያለው፣ ደፋር ሰው ነበር። ቶማስ ፊት ለፊት የሆነ፣ ቀጥተኛ፣ ታማኝና የራሱ የሆነ አቋም ያለው ሰው ስለሆነ፣ ሞት ፊት ለፊት ሲመጣበት እያየ ወደ ኋላ የሚያፈገፍግ ሰው አልነበረም። የእርሱ ታማኝነት፣ እውነተኛነት የተቀሩትን ደቀ መዛሙርት እንደሚያስፈራቸው፣ ወይም ለመሄድ ባይፈልጉም አብረውት እንዲሄዱ እንደሚያደርጋቸው እርግጠኞች ነን።

(2) ስለ ቶማስ ዮሐንስ ለሁለተኛ ጊዜ የጻፈው፣ ደቀ መዛሙርቱ ከክርስቶስ ጋር ፍሬ ነገር ባለው ውይይት ላይ በነበሩበት ወቅት ነው። በመጨረሻው እራት ላይ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፥

- *"ልጆች ሆይ! ከእናንተ ጋር ብዙ ጊዜ አልቆይም፥ እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፥ ለአይሁዳውያን ባለሥልጣኖች እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም እንዳልኳቸው፣ አሁንም ለእናንተ እንዲሁ እላችኋለሁ"* አላቸው (የዮሐ. 13፥33)።

ይህን ዓይነት አነጋገር ሁሉን ነገር ትተው ለተከተሉት ደቀ መዛሙርት በጣም አስደንጋጭ ነበር። አባባሉ ስላላስደሰታቸው ተቃውሟቸውን አሰሙ። ኢየሱስም የደነገጠውን ልባቸውን ለማረጋጋት፥

- *"ልባችሁ አይጨነቅ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም እመኑ፥ በአባቴ ዘንድ ብዙ መኖርያ አለ፥ አለበለዚያ ግን የምትኖሩበትን ስፍራ ላዘጋጅላችሁ እሄዳለሁ ባላልኋችሁም ነበር አላቸው"* (የዮሐ. 14፥1-2)።

### *፱-ሐ ቶማስ ጥሩ ጥያቄ ጠየቀ፥*

ኢየሱስ ስለምን እንደሚናገር ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የገባው አንድም ሰው አልነበረም። ብዙ ጊዜ የሰው ጸባይ ይህን ይመስላል። ድንቁርናችን እንዳይታወቅብን ሳይገባን የገባን አስመስለን ለማለፍ እንሞክራለን። ደቀ መዛሙርቱም ከእኛ የተለዩ አልነበሩም። በተፈጥሮው ቀጥተኛና እውነተኛ የሆነው ቶማስ ግን ሳይገባው የገባው መስሎ ለማለፍ ስለማይፈልግ አለማወቁን የሚያሳይ ጥያቄ ጠየቀ።

> *"...ጌታ ሆይ! ወዴት እንደምትሄድ አናውቅም፥ታዲያ መንገዱን እንዴት ማወቅ እንችላለን አለው"* (የዮሐ. 14፥5)።

ቶማስ *"ጌታ ሆይ! ስለምን እንደምትናገር ግራ ገብቶኛል፥ የምሄድበትን መንገድ ታውቁታላችሁ ትለናለህ፥ እንኳን መንገዱን ማወቅ ቀርቶ የት እንደምትሄድ እንኳን አናውቅም፥ ታዲያ መንገዱን እንዴት ማወቅ እንችላለን?"* ብሎ ጠየቀው። የቶማስ ጥያቄ መገለጥ ያለበትን ትልቅ የሕይወት ጥያቄ ለመግለጥ ምክንያት ሆነ። ማስመሰል የማይወደው ቶማስ ድንቁርናውን፣ ግራ መጋባቱን ሳይፈራና ሳይደብቅ በመግለጹ እንደሆነ ልብ እንበል። ቶማስ ኢየሱስን *"ጌታ ሆይ! ግራ ገብቶኛል፥ የተናገርከው አልገባኝምና አስረዳኝ"* አለው። ኢየሱስም ለጥያቄው አጥጋቢና ትክክለኛ የሆነ መልስ ሰጠው።

(3) ዮሐንስ ስለ ቶማስ ለሦስተኛ ጊዜ የተናገረው፣ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ላይ የተጠቀሰው ሀሳብ ነው። ቶማስ ስህተተኛ የሚያሰኘው፣ ተቀባይነት የሌለው አቋም የያዘ ነው ቢያሰኘውም፣ ሰዎች ስለ እርሱ ስለሚሰጡት መጥፎ ግምት ቅንጣት የሚያህል እንኳን ግድ ያለው ሰው አልነበረም። ኢየሱስ እንዲከተሉት የጠራቸውን ሁሉ ይወድ ነበር። በእምነታቸው የሚያሳዩትን ዕድገት በማየት ደስ ይለው ነበር። ሰዎች በቶማስ ሕይወት ውስጥ ማየት የቻሉት ደካማነቱን፣ የማያምን ወይም እምነት የጎደለውና ተጠራጣሪ ሰው መሆኑን ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን በቶማስ ሕይወት ውስጥ ያየው ያንን ብቻ ሳይሆን ሀቀኛነቱን (ኢንቲግሪቲውን) የሚጠብቅ ሰው መሆኑን ነው።





በዚህ ምክንያት ቶማስ የኢየሱስን ከሞት መነሳት ሲሰማ የተጠራጠረ መሆኑ ዓለምን ያስደነቀውና ያሳዘነው ይምሰል እንጂ ኢየሱስን አላሳዘነውም ነበር። ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ በሚጽፈው ታሪክ ወደ መጨረሻው ደርሶ ነበር። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በሞተ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተደነጋግጠውና ግራ ተጋብተው ስለ ነበረ፣ አብዛኛዎቹ ተበታትነው ነበር። ቶማስ የት እንደሄደ አይታወቅም ነበር። ምናልባት ሀዘኑን ለመወጣት ብቻውን ገለል ካለበት አንድ ሥፍራ ሄዶ ተቀምጦ ይሆናል። ሌሎችም ደቀ መዛሙርት እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ፈርተው ተሸሽገው እንደነበረ የታወቀ ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ከሞት የተነሳው ኢየሱስ መጀመሪያ ለአንዱ፣ ቀጥሎ ለሁለቱ፣ በመጨረሻም ለሁሉም ባልተጠበቀበትና ይሆናል በማይባልበት ወቅት ራሱን ይገልጥ ነበር። ቶማስ ከተቀሩት ደቀ መዛሙርት ጋር ስላልነበረ ኢየሱስን የማየት ዕድል አላጋጠመውም ነበር።

ኢየሱስን በቅርብ ከተከተሉት ደቀ መዛሙርት መካከል ሁለቱ ጴጥሮስና ቶማስ ይገኙበታል። አንደኛው የክርስቶስን ከሞት መነሳት ሲጠራጠር፣ ሌላው ደግሞ *"አላውቀውም"* ብሎ የከዳው ነው። የጴጥሮስ ችግሩ አለማወቅ፣ ማመን አለመቻል ሳይሆን ራሱን ከሞት ወይም ከችግር የሚያድን መስሎት ነው። የቶማስ ችግር ግን ያ አልነበረም። በመስቀል ሲሰቀል፣ በሚስማር ሲቸነከር፣ ጎኑ በጦር ተወግቶ ውሃና ደም ሲፈስው፣ በመጨረሻም "ተፈጸመ" ብሎ ሲሞት አይቶታል። ሬሳውን መቃብሩ ውስጥ ሲያኖሩት፣ ትልቅ ድንጋይ አንከባለው ሲዘጉበት አይቷል። ያ በድን እራሳ ድንጋዩን ገለባብጦ ይነሳል ብሎ መቀበል አዕምሮው *"ዕንቢ!"* ብሎት ነበር። ይሁን እንጂ፣ ቶማስ በሌለበት ቀደም ሲል እንደተናገረው በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነስቶ ደቀ መዛሙርቱ በአንድ ላይ በተሰበሰቡበት ወቅት ኢየሱስ በመካከላቸው በመገኘት ከሞት የተነሳ መሆኑን አረጋገጠላቸው። በተስፋ መቁረጥ የተሞላው ልባቸው እንደገና በተስፋ ተሞላ። ቶማስን ሲያገኙት፣ *"ጌታን እኮ አየነው"* አሉት። ቶማስም እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ *"ሃሌ ሉያ ጌታ ከሞት ተነስቷል"* አላለም። ነገር ግን፣

- *"በምስማር የተወጋውን እጆቹን ካላየሁና ጣቴን ካላገባሁ፤ እጄንም በጎኑ ቁስል ካላገባሁ አለምንም አላቸው"* (የዮሐ. 20፣ 25)።

እዚህ ላይ በግልጽ የቶማስን እውነተኛ ባሕሪ እናያለን። *"ጌታን አየነው"* ሲሉት፣ *"ምን ማለታችሁ ነው? የምትሉኝ አልገባኝም"* ሳይላቸው እንዳልቀረ እንገምታለን። ሳያውቅ እንዳወቀ፣ ሳይገባው እንደ ገባው ሰው አስመስሎ ለማለፍ የማይፈልግ ሀቀኛ ሰው መሆኑን በግልጽ እናያለን። ቶማስ አለመረዳቱን ብቻ ሳይሆን፣ ማመን የማይችል መሆኑንም አልደበቀም። *"በምስማር የተወጋውን እጆቹን ካላየሁና ጣቴን ካላገባሁ፣ እጄንም በጎኑ ቁስል ካላገባሁ አለምንም"* አላቸው። ቶማስ ደቀ መዛሙርቱ የነገሩትን የክርስቶስን ከሞት መነሳት ታሪክ የሰማው በጥር ጣሬ ተሞልቶ ነው። *"በጣም አዝናለሁ! ይሄን ዓይነቱ ነገር ፈጽሞ ሊሆን አይችልም። ደቀ መዛሙርቱ የፈለጋቸውን ይበሉ፥ የፈለጋቸውን ይመኑ እንጂ፣ እኔ በበኩሌ ይህን መቀበል ፈጽሞ አልችልም፤ እነርሱ የሚያወሩት እንዲሆን የሚፈልጉትን ምኞታቸውን ይሆናል"* የሚል ይመስላል። ኢየሱስን አየነው ሲሉ፣ ማየታቸውን አልተጠራጠረም። ይሁን እንጂ፣ በበኩሉ ተነስቷል ብሎ ማመን አልቻለም ነበር። እያስመሰለ የማያምነውን "አምናለሁ" ማለት የሚፈልግ ሰው አልነበረም። ብዙዎቻችን በቀላሉ የምንሳብ፣ በቀላሉ ከመሥመር የምንወጣ፣ ማንም ሰው ሊያሞኘን ስለ ሚችል፣ በመካከላችን ቶማስን የመሳሰሉ ብርቱ ሰዎች ያስፈልጉናል።

የሚያስደንቀው ነገር፣ *"በሚስማር የተወጋውን እጆቹን ካላየሁና ጣቴን ካላገባሁ፣ እጄንም በጎኑ ቁስል ካላገባሁ አለምንም"* ቢልም፤ የተቀ ሩት ደቀ መዛሙርቱ *"ለምን አላመንክም? እምነት የሌለህ ደካማ ክርስ ቲያን ነህ"* በማለት አልኮነኑትም። እንዲሁም ከማህበራቸው አላስወጡ ትም። ሌላው ቀርቶ እንዲያምን ብለው አልተከራከሩትም ነበር። ይህን ያላደረጉትም በማስገደድ ወይም በማስፈራራት ሌላውን ለማሳመን መሞከር ትክክል አለመሆኑን ስለሚያውቁ ነው። ኢየሱስ ቶማስን *"ብታ ምን እመን፥ ባታምን የራስህ ጉዳይ ነው"* ብሎ ቶማስን ያልተወው፣ የቶማስ ጥያቄ እውነተኛና ከልቡ የወጣ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው።





የቶማስን የአዕምሮ ውስንነትን ስለተረዳ ነው። ሰው እግዚአብሔር ወዶ ራሱን ካልገለጸለት በስተቀር፣ ሰው በግሉ እግዚአብሔርን ፈልጎ ማግኘት እንደማይችል ስለሚያውቅ ነው። ቶማስ ኢየሱስን በግል አይቶው በደስታ ከሚያጨበጭቡት ጋር መስሎ ማጨብጨብ አልፈለገም። *"የማያምን ክር ስቲያን፣ ያልተፈታ ክርስቲያን፣ ያልተቀባ ሰባኪ"* በማለት ይተቹኛል፣ የቅጽል ስም ያወጡልኛል ብሎ አልፈራም። የማያምነውን ሌሎችን ደስ ለማሰኘት፣ ወይም ለመምሰል ሲል ብቻ "አምናለሁ" ለማለት አዕምሮው እምቢ ስላለው ነው።

(4) ዮሐንስ ስለ ቶማስ ለአራተኛ ጊዜ የተናገረው፣ ክርስቶስ ራሱን ለቶማስ እንደገና በገለጸበት ጊዜ የሆነውን በመጥቀስ ነው። እግዚአ ብሔር የቶማስን እውነተኛነት፣ ሀቀኛነት፣ አስመሳይነት የሌለበትን ሕይ ወት ስላደነቀ ከአንድ ሳምንት በኋላ ለቶማስ ሲል ብቻ እንደገና ቶማስ በተገኘበት ስብሰባ ላይ ራሱን እንደገና ገልጦ ቶማስን፣

- *"ጣትህን ወዲህ አምጣና እጆቼን እይ፥ እጅህንም አምጣና በጎኔ ውስጥ አግባው፥ እመን እንጂ እምነተ ቢስ አትሁን አለው"* (የዮሐ. 20፣27)።

ቶማስ ሌላውን ኮፒ አድርጎ *"ሃሌሉያ"* ብሎ የሚያጨበጭብ፣ የራሱ የሆነ አቋም የሌለው ሰው አልነበረም። *ከሞት የተነሳውን ኢየሱስ በራሱ ዓይን ካየ በኋላ "የእኔ አምላክ! የእኔ ጌታ"* ብሎ ጮኸ። እኛም ልባችን በጥያቄና በጥርጣሬ የሚሞላበት ጊዜ፣ ለማመን እየፈለግን ማመን የሚያቅተን፣ የእግዚአብሔርን ደግነት ማየት ፈልገን አልታይ የሚለን፣ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ናፍቀን መስማት የማንችልበት፣ ሁሉ ነገር ጨለማ የሚሆንብን ጊዜ አለ። አዕምሯችን በጥያቄ ቢሞላ እግዚአ ብሔር እኔና እናንተን በውስጣችሁ ጥያቄ ለምን ተፈጠረ ብሎ አይቀየ መንም። ቅር የሚለው *ካርቦን-ኮፒ* ስንሆን፣ የራሳችን አቋም ሳይኖረን ከሚፈሰው ጋር አብረን የምንፈስ ሆነን ሲያገኘን ነው። ዝም ብለን ከመፍ ሰስ፣ *"ጌታ ሆይ! አለማመኔን እርዳ"* ብንለው፤ አስፈላጊ ለሆነው ጥያቄ ያችን መልስ ይሰጠናል። በዙሪያችን የከበበንን ጨለማና ደመና፣ እንቅፋ

ትና እሾህ አጥፍቶ እንደገና በእርሱ ተስፋና ሰላም ሊሞላን፤ ሕያውነቱንም ሊያረጋግጥልን ይችላል። ካልገባን መጠየቅን፣ የሚያጠራጥር ነገር ሲያጋጥመን መጠራጠርን አንፍራ። መጠንቀቅ ያለብን፤ የራሳችን አቋም ሳይኖረን ካርቦን ኮፒ ወይም ግልባጭ ክርስቲያኖች እንዳንሆን ነው።



2

# ካርቦን-ኮፒ መሆናችን፣ ራሳችንን በመጥላታችን ይሆን?

አሜሪካ ውስጥ የምንኖር ኢትዮጵያውያን አማኞች፣ የአሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት የሚያልፉበትን ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች እንዳሉባቸው በመጠኑም ቢሆን እናውቃለን። በሌላ በኩል ግን ለወንጌል ሥርጭት ሊረዳቸው የሚችሉ ብዙ መልካም የሆኑ ነገሮች አሏቸው። ይኸውም፣ ያማረ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ፣ ብዙ ገንዘብ፣ መንፈሳዊ አገልጋዮቻቸውንና መሪዎቻቸውን ለአገልግሎት የሚያዘጋጁበትና የሚያሰለጥኑበት አያሌ መንፈሳዊ ኮሌጆችና ሴሚናሪዎች አሏቸው። ቁጥር ስፍር የሌላቸው መንፈሳዊ መጽሐፍት፣ ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ብዙ መንፈሳዊ ድርጅቶች አሏቸው። ወንጌልን በፈለጉት ዓይነት ለመስበክ ሙሉ የሃይማኖት ነጻነት አላቸው። ወንጌልን በማሰራጨታቸው ምክንያት በመከራና በስደት ውስጥ አያልፉም። ይሁን እንጂ፣ እውነተኛነት የሌለው የክርስትና ሕይወት አኗኗራቸው፣ ያላቸውን አገልግሎታቸውንና ምስክርነታቸውን ሲያበላሽባቸው እናያለን።

## *1. ክርስቲያን "እውነትን" ይዞ ለምን አይቆምም?*

የክርስትና እምነት "እውነት" በሆነው በክርስቶስ ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ ክርስቲያኖች እውነትንነት የሌለው፣ አንድ ወጥ ያልሆነ ወይም በማ

*ስመሰል ሕይወት ውስጥ ለምን ይኖራሉ? ኢየሱስ በእርሱ ላመኑት አይሁዳውያን፣*

- *"እውነትን ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኋል" አላቸው (ዮሐ. 8፥32)።*

የክርስትና እምነት መሠረቱ፣ *"እኔ እውነት...ነኝ"* ባለው ክርስቶስ ላይ ከሆነ፣ ይህን እውነት ያወቁ ክርስቲያኖች እውነትን ይዘው የማይሄዱት፣ ወይም በእውነት ውስጥ የማይኖሩት ለምንድነው? ከክርስቶስ ጋር እውነተኛ የሆነ አንድነት መሥርተው ከእርሱ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ለመፍጠር፣ አንድነቱን ለማዳበር፣ ለምን ያቅታቸዋል? ከሰዎች ጋር እውነትነት ያለው ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሁሉም ጥማት እንደሆነ እናምናለን። የእግዚአብሔርም ፍላጎት ይሄው ነው። ይሁን እንጂ፣ በእውነት ለመኖር ያልቻሉበት ምክንያት ምን ይሆን? በእውነት ውስጥ ለመኖር ራስን ማለማመድን ይጠይቃል።

ከሰው ጋር ለሚኖረን መልካም ግንኙነት *"እውነተኛነት"* ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን። ይሁን እንጂ፣ ይህ እንዳይሆን የተለያዩ ዕንቅፋቶች ያጋጥሙናል። ዕንቅፋት ከሚሆኑብን ምክንያቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፣ ለራሳችንና ለእግዚአብሔር እውነተኞች አለመሆናችን ነው። ብዙዎቻችን ከሰው ጋር በሚኖረን ግንኙነት የምንገልጸው ከውስጣችን ያለውን ሃሳብ ወይም ስሜት እውነተኛውን አይደለም። ሁላችንም የሚሰማንን እውነተኛውን የማንገልጽበት የራሳችን የሆኑ ምክንያቶች አሉን። ለምሳሌ፥ ውሃ ቀጠነ የሚለውን አለቃውን፣

> *"አለቃዬን የሚሰማኝን እውነቱን ብነግረው ከሥራ ያስወጣኛል..."* በማለት ስሜቱን ደብቆ ይኖራል።
>
> *ቤት ውስጥ የባሏን ዕርዳታ የምትፈልገዋ ሚስት "ሁለታችንም እኩል ሠርተን ወደ ቤታችን ስንገባ፣ እቤት ያለውን ሥራ አብረን እንስራ ብለው ያስቆጣዋል ብዬ እፈራለሁ..." በማለት የሚሰማትን ስሜት አፍና ይዛ ትኖራለች።*





> *የሚስቱን የፍቅር መግለጫ ያጣ የመሰለው ባል "ሚስቴን 'አትክላከሉ' የሚለውን ትዕዛዝ ችላ ብለሽዋል ብላት የበለጠ ከእኔ ትሸሽ ይሆናል ብዬ እፈራለሁ..." በማለት በውስጡ የሚሰማውን ስሜት አይገልጽም።*
>
> *በመጋቢው ደስ ያልተሰኘ ምዕመን "የቤተ ክርስቲያን መጋቢዬን 'ዕርዳታህን ፈልጌ ማግኘት አልቻልኩም' ብለው አስቆጣው ይሆናል ብዬ እፈራለሁ..." በማለት ስሜቱን ደብቆ ይኖራል።*

በዚህ ዓይነት ብዙዎቻችን ከውስጥ የሚሰማንን እውነተኛውን ስሜታችንን ገልጸን አንናገርም። የዚህ ዋናው ምክንያት ሰውን ሁሉ ለማስደሰት እንጂ ቅር ለማሰኘት ስለማንፈልግ ነው። አንድ ጸሀፊ፣

- *"ሰውን ሁሉ ለማስደሰት ሲል ራሱን የሚከረክም መጨረሻ ላይ ማንነቱን ያጣል"* አለ።

የሰው ሁሉ ፍላጎት የተለያየ ስለሆነ፣ አንዱን ያስደሰት፣ ሌላውን ያስቀይማል። በየጊዜው አቋማችንን ሳንለዋውጥ ሰውን ሁሉ ለማስደሰት፣ ፍላጎቱን ሁሉ ለማሟላት አንችልም። ሁሉንም ለማስደሰት የምንወስደው ዕርምጃ ደግሞ አቋም-የለሽ እንደሚያደርገን ግን የተገነዘብነው አይመስለንም።

ሰው ሁሉ በእኛ ደስ እንዲለው ፍላጎታችን ከሆነ፣ የሚጠይቁንን ሁሉ ለማሟላት ከመስመራችን ያስወጣናል። ያም ሆኖ *"አስደስተዋለሁ"* ብለን ያሰብነውን ሰው በማናውቀው ምክንያት ልናስቀይመው እንችላለን። *"ሌላውን አስቀይም ይሆናል"* የሚል ፍርሃት የሚያጠቃን ከሆነ፣ ለምሳሌ አንድ ሰው እግራችን ላይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ቢቆም፣ *"እባክህን እየረገጥከኝ ነውና እግርህን ከእግሬ ላይ አንሳ"* ብለን ለመናገር ድፍረት አይኖረንም። በዚህ ምክንያት የውስጥ ስሜታችንን ደብቀን ለረጅም ጊዜ እየተረገጥን እንቆያለን። ይሄም እውነተኞች አለመሆናችንን ብቻ ሳይሆን፣ ጉዳት ላይ የሚጥለን መሆኑን ማወቅ አለብን። ስሜታችንን ደብቀን እውነት ያልሆነውን ከመናገር ይልቅ፣ ሁልጊዜ እውነቱን በፍቅር እንድንናገር መጽሐፍ ቅዱስ ይመክረናል፥

- *“እውነቱን በፍቅር እየተናገርን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር እናድጋለን” (ኤፌ. 4፥15)።*
- *“ስለዚህ ውሸት አትናገሩ! ሁላችንም የአንድ አካል ክፍሎች ስለ ሆንን እርስ በርሳችን እውነት እንናገር” (ኤፌ. 4፥25)።*

እውነተኛ መሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ብናውቅም፣ ከሚመለከተው ሰው ጋር ፊት ለፊት ስንገጥም ይህንን አሳባችንን ተግባራዊ ለማድረግ ከባድ ይሆንብናል። ስለዚህ እውነቱን ብንናገር እውነቱን ለመስማት ፈቃደኛ አይሆኑም ይሆናል ብለን በማሰብና በመፍራት ሁል ጊዜ የምንናገረው በልባችን ውስጥ ያለውን እውነቱን አይደለም። ለምሳሌ እንግዳ ሆኖ ከሰው ቤት ቢሄድ፣ ረሃብ አቃጥሎት “ምሳ ብላ” ቢባል፣ ስሜቱን ደብቆ “አልበላም! ጠግቤአለሁ! የበላሁት ቅርብ ጊዜ ነው” በማለት ይዋሻል። ይህ ችግር የባህል ተጽዕኖ ያመጣብን ይሆን?

## *2. ራሱን የሚወደው ሰው፣ ሌላውን ለመሆን ለምን ይፈልጋል?*

- *ጥዋት ከእንቅልፋችን ተነስተን ፊታችንን በመስታወት ስናይ የለመድነውን፣ የምናውቀውን የራሳችንን ፊት በማየት ፈንታ የሌላውን ሰው ፊት ብናይ፣ ምንም ያህል የምናደንቀው ሰው ፊት ቢሆንም፣ ያየነው መልክ አስደስቶን “ሃሌ ሉያ! እከሌን ሆንኩ!” በማለት ፈንታ “ምን ሆንኩ? ምን ነካኝ?” ብለን በመደንገጥ ራሳችንን መጠየቃችን አይቀርም። በዚህ ዓይነት ሁላችንም ራሳችንን እንጂ ማንንም መሆን አንፈልግም። ይህ እውነት ከሆነ፤ ታዲያ ራሳችንን መሆን ትተን ሌላውን ለመሆን ወይም ለመምሰል የምንጥረው ለምን ይሆን? ራሳችንን ጠልተን፤ በእኛ ውስጥ ያለውን ነገር መቀበል አቅቶን ይሆን? እግዚአብሔር የፈጠረን መልካም ሆነን እንድናድግና እንድንለመልም ነው። መልካም ሆኖ ማደግና መለምለም የምንችለው ራሳችንን ሆነን እንጂ፣ ሌላውን ሆነን ወይም መስለን ብናድግ ደስተኞች እንደ ማንሆን የታወቀ ነው።*





እግዚአብሔር ማናችንንም ካርበን-ኮፒ ወይም የሌላው ሰው ግልባጭ አድርጎ አልፈጠረንም። እያንዳንዳችንን ልዩ አድርጎ የፈጠረን በመሆኑ፣ ሌላውን ለመሆን ምንም ያህል ጥረት ብናደርግ መሆን አንችልም። የተፈጠርንበትን ዓላማ ለመፈጸም፣ ወይም እኛ እንድንሠራው የተመደበልንን ሥራ ለመሥራት፣ ከእኛ የተሻለ ሰው እንዳይኖር አድርጎ፣ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ሰጥቶ ፈጥሮናል። የብዙዎች የጭንቀት ምክንያት በራሳቸው እምነት ያጡ በመሆናቸው፣ ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌላውን ለመሆን ስለሚሞክሩ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲሠራ፣ በሥራው ላይ ድግግሞሽ የለበትም። አንድ መለሰ ወጉ ሠራ እንጂ፣ ሁለት መለሰ ወጉምችን አልሠራም። ቢፈልግ መሥራት ያቅተዋል ማለቴ አይደለም። እግዚአብሔር በሕይወታችን ዓላማና ዕቅድ ካለው፣ ሌላውን ለመሆን ስንሞክር፣ *“የእግዚአብሔር ዓላማና ዕቅድ በሕይወቴ እንዲፈጸም አልፈልግም”* ማለታችን እንደሆነ ብዙዎቻችን የተረዳነው አንመስልም።

ተፈጥሯችንን ይዘን እንዳንቀጥል፣ የሆንነውን እንዳንሆን እንቅፋት ከሚሆኑብን ልዩ ልዩ ምክንያቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፣ ስለ ራሳችን ዝቅተኛ የሆነ አስተያየት ስላለን ነው። እግዚአብሔር ልዩ አድርጎ እንደፈጠረን፣ ዓላማውና ዕቅዱ በሕይወታችን እንዲፈጸም እርሱ ራሱ የሚያግዘን መሆኑን ያልተረዳን ከሆነ፣ ለራሳችን የሚኖረን አስተያየት ዝቅተኛ ነው። ገና በእናታችን ማህጸን ውስጥ ከመጸነሳችን በፊት እግዚአብሔር ለያንዳንዳችን ልዩ ዓላማ እንዳለው ስንገነዘብ፣ ሕይወታችን በእግዚአብሔር ፊት ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው እንረዳለን። እግዚአብሔር ዓላማውን መፈጸም እንድንችል ለሥጋዊ አካላችን አስፈላጊውን ኃይል፣ የመፍቀድና የማቀናጀት ችሎታ ሰጥቶናል። ስሜቶቻችንን በአግባቡና በመልካም ሁኔታ መጠቀም የምንችልበትን ዕውቀት፣ እንዲሁም ለመውደድም ሆነ ለመወደድ የሚያስችል አቅም ሰጥቶናል። ማሰብ፣ ማመዛዘንና ማስታወስ እንድንችል ጥሩ አዕምሮ ፈጥሮልናል። ሃሳባችንን በቃላትም ሆነ ያለቃላት ለመግለጽ፣ ከሰው ጋር ለመነጋገር፣ አቅምና ችሎታ ሰጥቶናል። በተጨማሪ መንፈሳዊ ዝንባሌ፣ ይኸውም እግዚአብሔርን የማወቅና እርሱን የመፈለግ፣ ከእርሱ ጋር ሕብረት

ለመፍጠር ዕርምጃ እንድንወስድ የሚያደርግ መንፈሳዊ ጥማትን በውስጣችን አኑሯል።

## *3. አንዳንድ ሰዎች እንድንሆንላቸው የሚፈልጉት ነገር አለ፥*

ብዙዎች በሕይወታችን እንድንሆን የሚፈልጉት ወይም የሚመኙት ነገር አለ። ለምሳሌ፣ ልጆቻችን ሁልጊዜ ቴሌቪዥን የማየት ነጻነት እንዲኖራቸው፣ ነጻነት የምንሰጥ ወላጆች እንድንሆንላቸው ይፈልጋሉ። የሥራ አለቃችን በሥራችን ፍሪያማ እንድንሆን ይፈልጋል። ገንዘብ አበዳሪ ኩባንያ ብዙ ትርፍ እንዲያገኝ፣ ለእኛ ያሰበና የተቀረቀረ መስሎ ሁልጊዜ እንድንበደር፣ ከብድር እንዳንወጣ ይፈልጋል። የሬስቶራንት ባለቤቶች ብዙ በመብላት የሚፈጠረውን ችግር ቢያውቁም፣ ብዙ እንድንበላ ይፈልጋሉ። የሕግ ባለሞያ ከከሳሻችን ወይም ከተጋጨነው ሰው ጋር ያለን ጉዳይ በአጭሩ እንዳይቀጭ፣ ቶሎ እንዳንስማማ ይፈልጋሉ። ሁሉም ለእኛ ያሰቡልን ይምሰሉ እንጂ፣ የራሳቸው የሆነ አጀንዳ አላቸው። ሰዎች እንድንሆን የሚፈልጉትን ዓይነት ሰው ለመሆን የምንሞክር ከሆነ፣ ነጻ ሆነን ራሳችንን ለመሆን አቅም ያንሰናል። ምንም ያህል ብንወዳቸውም፣ እንድንሆንላቸው የሚፈልጉትን ሁሉ መሆን አንችልም። ሰዎች እንድንሆን የሚፈልጉትን ለመሆን ሙከራ ማድረግ ባዶ ሕይወት መኖርን መምረጣችን ይሆናል። ምን መሆን እንዳለብን ከእግዚአብሔር በቀር በደንብ የሚያውቀን፣ ወደምን መለወጥ፣ እንዲሁም እንዴት መለወጥ እንዳለብን ሊነግረን የሚችል ሰው በዓለም ላይ አንድም የለም። መለወጥ ቢያስፈልገን ዘላቂ የሆነ ለውጥ ማምጣት የምንችለው የእኛ ፈቃድ ሲኖርበት ብቻ ነው።

> *ኔልሰን ማንዴላ፣ በደቡብ አፍሪካ የነበረውን የዘር አድልዎ በመቃወሙ ታሥሮ ሮቤን ደሴት ውስጥ በተጣለበት ረጅም ዘመን፣ አሰሪዎቹ "ቁምጣ ሱሪ" እንዲለብስ አድርገውት ነበር። ይህን ያደረጉበት ምክንያት መለያው ሙሉ ሰው በመሆን ፈንታ ልጅ እንዲሆን ነው። ያሠሩት ባለሥልጣናት ለዘረኛው ሕብረተሰብ ጸጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ፣ ከእርሱ ጋር*





> *ይሰቃዩ የነበሩት ሰዎች ቁጠኛና በጥላቻ የተሞሉ ሆነው የበቀል እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነበር። ማንዴላ እንዲሆን የሚፈልጉትን አልሆንላቸውም።*
>
> *ማንዴላ በሃያ ሰባት ዓመት የእስራት ዘመኑ በጣም ቢሰቃይም፣ በሕይወቱ ብዙ የተማረና ያደገ ሰው ሆነ። የታሠረበትን ወህኒ ቤት "ዩኒቨርሲቲ" ብሎ ጠራው። ለፍትህ ሙሉ በሙሉ ራሱን የሰጠ መሆኑ ብቻ ሳይሆን "ጥላቻን" የሚቃወም ሰው ሆነ። ወህኒ ቤት ሳለ ይጠብቁት የነበሩት ዘቦች እንኳን በሕይወቱ ተሰበው ነበር። ማንዴላ ከእስር ቤት ወጥቶ "ፕሬዚደንት ማንዴላ" ሆኖ በሰላምና በእርቅ መንፈስ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መመሪያ ተከትሎ ደቡብ አፍሪካን ወደ ሰላምና ፍቅር መራ።*

እግዚአብሔር እኔና እናንተን ኔልሰን ማንዴላን እንድንሆን አልፈጠረንም። የፈጠረን ራሳችንን እንድንሆን ነው። ራሳችንን በራሳችን ስላልፈጠርን እኛም ብንሆን እንዴት መለወጥ እንዳለብን ለራሳችን መንገር አንችልም። ከእኛ የሚጠበቀው ሌላውን መውደድ፣ መሆን የሚችሉትን እንዲሆኑ መርዳት ነው። መለወጥም ሆነ መሆን የምንችለውን እንድንሆን ማድረግ የሚችል ከእግዚአብሔር በስተቀር በዓለም ውስጥ ሌላ ሰው የለም። እግዚአብሔር እኛን እንድንሆን የሚፈልገውን ከማድረግ ውጪ ሌላ ዓላማ የለውም። የእኛን ዕርዳታ አይፈልግም።

## *4. የሌላውን ሰው ልምምድ ኮፒ በማድረግ የሚዋሹ አሉ፥*

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ሆነ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሰው በራሱ ጥረት የሚያገኘው እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ታዲያ ከላይ ያየናቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ አስፈላጊነቱ ለብዙዎች ለምን አይታያቸውም? እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ፣ ይኸው ሰዎች እውነቱን እስኪያውቁ ድረስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ኮፒ አድርጎ "ስጦታው አለኝ" ማለት ይቻላል። በዘመናት ብዙዎች ስጦታው ሳይኖራቸው "አለን" በማለት ከብረውበታል፥ እጅግ በጣም ታውቀውበታል። ጥንት ብቻ ሳይሆን፤ ዛሬም የሌላውን ሰው ልምምድ

ኮፒ እያደረጉ ክርስቲያን የሆንነውን ሁሉ የሚያሳፍር አሳዛኝ ነገሮችን ሲለማመዱ እናያለን።

የሌላውን ሰው ልምምድ የራሳቸው አድርገው ሲለማመዱ ማየት በአሁኑ ጊዜ አዲስ አይደለም። እንዲህ ዓይነቶቹን ለማየት ብዙ ርቀን መሄድ አያስፈልገንም። አሜሪካን አገር የምንኖር በየቀኑ በቴሌቪዥኖናችን እስክሪን ላይ እናያቸዋለን። በበኩሌ የሚያሳዝነኝ እነዚህ ደፋር የሆኑ ሰዎች በእግዚአብሔር ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚነግዱ፣ ሀብታም ለመሆን የሚሞክሩት አይደሉም። እነዚህ ሰዎች የሚያደርጉት ልምምድ እውነትነት የሌለው መሆኑን ለመረዳት ይህን ያህል "የኑክሌር ፊዚስት" "የአንጎል ቀዶ ጥገና ሀኪም" መሆንን አይጠይቅም። እኔን የሚገርመኝና የሚያሳዝነኝ እነዚህን እውነትነት የሌላቸውን ሰዎች ቴሌቪዥን ውስጥ ያዩዋቸውን ሰባኪዎችን ኮፒ አድርገው፣ ፍጹም የዋህና ያልተማረውን፣ መጠየቅና መጠራጠር ኃጢአት የሚመስለውን ሕዝባችንን በተራቸው ለማታለል የሚሞክሩ መሆናቸው ነው።

አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ የዋህ ስለሆነ፣ አንዳንድ ልምምዶች ከየት ኮፒ እንደሚደረጉ የማወቅ ችሎታ ስለሌላቸው በክርስቶስ ስም፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሰጡትን ሁሉ "እውነት ነው" ብሎ ይቀበላል። "ጌታ አዲስ መገለጥ ሰጠኝ" ይበሉ እንጂ፤ አብዛኛው ከሌላው ሰው ልምምድ የተቀዳ ወይም ኮፒ የተደረገ ነው። ለዚህ አንድ ጥሩ ምሳሌ ልንገራችሁ።

> *ከረጅም ዘመን በፊት አገራችን ውስጥ "ዲሞኖሎጂ" በማለት የታወቀ አንድ ልዩ እምነት ብቅ ብሎ ነበር። ይሄም "ክርስቲያን የሆነ፤ ደህንነቱን በደንብ ያረጋገጠ ክርስቲያን፣ በአጋንንት መንፈስ ሊሞላ ይችላል፥ አጋንንቱም የሚወጣው በተውኪት፣ በተቅማጥ ነው" የሚል ትምህርትና እምነት ነበር። በወቅቱ የነበርነው አስተማሪዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁኔታው አስደንግጦን "መንፈስ ቅዱስና አጋንንት ደባል ሆነው አብረው መቀመጥ አይችሉም" በማለት ተሯሩጠን በማስተማር ትምህርቱና ልምምዱ ወዲያው እንዲቆም ተደረገ። ይህን ዓይነቱን አዲስ እምነት ካመጡት ሰዎች መካከል አንደኛው በቅርብ ጊዜ የሞቱት እንግሊዛዊው ዴሪክ ፕሪንስ የተባሉት ሰው ነበሩ። እኚህም ሰው ስለዚህ አዲስ ትምህርትና ልምምድ መጽሐፍ ጽፈው ነበር። ዴሪክ ፕሪንስ ከጥቂት ዓመት በኋላ ከመስመር የወጣ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ትምህርት ማስተማራቸውን ተገንዝበው፣ ንስሀ ገብተው አቋማቸውን አስተካከሉ። ይሁን እንጂ፣ ቀደም ሲል የጻፉት መጽሐፍ በየቦታው ተበትኖ ብዙ ሰዎች እጅ ገብቷል። ዴሪክ ፕሪንስ አቋማቸውን ያስተካከሉ መሆናቸውን ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች ያ ቀደም ሲል የጻፉት መጽሐፍ በእጃቸው ሲገባ፣ ያንን ኮፒ በማድረግ "እግዚአብሔር አዲስ መገለጥ ሰጠኝ" ብለው የተሳሳተ ትምህርት የሚያስተምሩ አሉ።*





እኛ ይህንን እንግዳ ትምህርት ለማስተካከል በምንሯሯጥበት ዓመት የተወለደ ልጅ አድጎ፣ ሠላሳ ዓመት ሆኖት ዛሬ የአንድ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆኖ ሲያገለግል አጋጠመኝ። ይህ ወጣት ፓስተር "ጌታ አዲስ መገለጥ ሰጠኝ" ብሎ "የዲሞኖሎጂ" ትምህርት ያስተምራል። የዚህ ትምህርት መሥራች የሆኑት ዴሪክ ፕሪንስ በዚህ ነጥብ ላይ የነበራቸውን አቋም ያስተካከሉ መሆኑን ያ ወጣት አያውቅም። ያሳዘነኝ በዚያ ወጣት መጋቢ ሥር የሚገለገሉት አማኞች ናቸው። ትምህርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለመሆኑን የመመርመር ችሎታ ወይም አቅም የላቸውም። የሰጧቸውን ሁሉ "አሜን" ብለው አጨብጭበው የሚቀበሉ ናቸው። ሌላው የሚያሳዝነው ነገር፤ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ያለአባት ያደጉ ክርስቲያኖች መኖራቸው ነው። ይህን ወጣት መጋቢ "በጌታ ያሳደገህ ማን ነው?" ብዬ ጠየቅሁት።

*ጳውሎስ "ከማንም አልተማርኩም" ያገኘሁት መገለጥ ከላይ ነው"* ሲል አባባሉን በደንብ ያልተረዱ፣ አንዳንድ አማኞች ዛሬ *"ማንም አላስተማረኝም፤ መንፈስ ቅዱስ ነው አስተማሪዬ"* የሚሉ፣ በመንፈሳዊ ሰው እግር ሥር ቁጭ ብሎ መማር ማነስ የሚመስላቸው ሰዎች የበዙበት ዘመን ነው። ያም ወጣት ፓስተር "በጌታ ያሳደገህ ማን ነው?" ብዬ ለጠየቅሁት

መልስ ሲሰጠኝ፣ እንደገመትኩት "ከማንም አልተማርኩም፥ የአንዳንድ ሰዎችን መጽሐፍ እያነበብኩ ነው ያደግሁት" አለኝ። እኔም ቀጥዬ፤ "የነማንን መጽሐፍ ነው ያነበብከው?" ብዬ ለጠየቅሁት መልሱ፤ "የነዴሪክ ፕሪንስን" መጽሐፍ ነው" አለኝ። እኔም በድፍረት "ዴሪክ ፕሪንስ ድሮ የጻፉትን መጽሐፍ አንብበህ እንደሆነ፣ ያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፥ እሳቸውም ንስሀ ገብተው አቋማቸውን አስተካክለዋል። በጌታ የዳነ ክርስቲያን ወደ ኋላ በፈቃዱ ካልተመለሰ በስተቀር፣ በአጋንንት ሊሞላ አይችልም። ሰይጣን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ደባል ሆኖ መኖር አይችልም" በማለት ላስረዳው ሞከርኩ። የሚያሳዝነው ያ ወጣት የምነግረውን መስማት ፈቃደኛ አልነበረም። የእርሱን ዓይነት አቋም የሌለውን ሁሉ፣ "የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ" የሚል የቅጽል ስም ሰጥቶ ስህተት የሆነውን ልምምዱን ይቀጥላል። ማን ቢነግረው ይሰማ ይሆን? ዴሪክ ፕሪንስ ከመቃብር ተነስቶ ካልነገረው ሌላ ሰው ቢነግረው ይሰማል ብዬ ማመን ይከብደኛል።

የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ባለበት ጊዜና አካባቢ ብዙ ጊዜ እውነት ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችና ልምምዶች ይታያሉ። የእግዚአብሔር ኃይል ሳይሰማቸው በማስመሰል ብቻ "ተሰማን" የሚሉ አሉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በመኖራቸው ብቻ "መንፈስ ቅዱስ በዘመናችን አይሠራም" ብሎ መደምደም ትክክል አይደለም። ይሁን እንጂ፤ የሚነግሩንን "አሜን" ብለን ከመቀበላችንና የልምምዱ ተካፋይ ከመሆናችን በፊት፤ ብዙ እውነት መሳይ ልምምዶች አሉና በጥንቃቄ መመርመር አለብን። የትንቢት ስጦታ ሳይኖራቸው ትንቢት የሚተነብዩ፣ የቋንቋ ስጦታ ሳይኖራቸው በቋንቋ እንናገራለን የሚሉ፣ የመተርጎም ስጦታ ሳይኖራቸው እንተረጉማለን በማለት ተነስተው የፈለጉትን የሚናገሩ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም የበለጠ የበዙበት ዘመን ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል።

ይህን ታሪክ አንዳንዶቻችሁ ሳትሰሙት እንዳልቀራችሁ እምናለሁ። በአንድ ስብሰባ ላይ አንዲት ሴት ትንቢት ለመናገር በሕዝቡ መካከል ቆማ በኃይልና በታላቅ ድምጽ፣ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ሙሴ የምድር እንስሶችንና አራዊቱን እየመራ ወደ መርከቡ





እንዳስገባ፣ ሕዝቤ የሆናችሁትን በእኔ ከታመናችሁብኝ በጎ ወደ ሆነው ነገር እመራችኋለሁ" አለች። ሕዝቡም ይህን ሲሰማ እንዱ አጠገቡ ያለውን ሰው "...ሙሴ ነው ያለችው እንዴ?" እያለ ሌላውን መጠየቅ ጀመረ ። ከእግዚአብሔር ተሰጠኝ ያለችውን መልዕክት ተናግራ ሴትዮዋ ቁጭ አለች። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ እንደገና ተነስታ አሁንም በኃይለኛ ቃል "የሠራዊት ጌታ እንዲህ ይላል፥ ቅድም የነገርኳችሁ ተሳስቼ ነው፥ ሙሴ ሳይሆን ኖህ ነው ይላል የሠራዊት ጌታ" ብላ ተቀመጠች።

ለምን ይሆን አንዳንድ አማኞች የራሳቸው ያልሆነውን፤ እውነትነት የሌለውን ነገር ከሌላው ኮፒ አድርገው የሚለማመዱት? አብዛኛዎቹ ሕዝቡ ምን መስማት፣ ምን ዓይነት ነገር ማየት እንደሚፈልግ ስለሚያውቁ፣ ሕዝቡ መስማት የሚሻውን እንዲሰማ ካደረጉት፣ ብዙ ተከታዮችና አድናቂዎች ማግኘት እንደሚያስችላቸው ስለሚያውቁ ነው። ክርስትና ዋጋ እንደሚያስከፍል፣ መስቀል ያለበት ሕይወት፣ መንገዱ ጠባብ የሆነ መሆኑን በግልጽ ቢያስተምሩ አድናቂና ተከታይ የማይኖራቸው መሆኑን ስለሚያውቁ፣ ሕዝቡ የሚፈልገውን ዓይነት ትምህርት ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ።

ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ አንድ ጊዜ ከአምትስ ሺ ሕዝብ በላይ ተከታይ ነበረው። የተከተሉትም የሠራውን ተአምር፣ ይኸውም በአምስት እንጀራና በሁለት አሣ አምስት ሺ ሕዝብ አብልቶ ያጠገበ መሆኑን በማየታቸው ነበር። ይህን የመሰለ አስደናቂ ተአምር ካዩ በኋላ፣ ኢየሱስ ሲያስተምር፣ እርሱን ለመከተል፣ ደቀ መዛሙርቱ ለመሆን ከመረጡ፣ እርሱን መከተል ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍላቸው በግልጽ ነገራቸው እንጂ፣ እውነቱን አልደበቃቸውም። ክርስቶስን መከተል የሚያስከፍለውን ዋጋ በስፋት ከሰሙ በኋላ፣ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ብቻ ሲቀሩ ሁሉም ትተውት ሄዱ። ይህን ተመልክቶ ወደ ቀሩት ደቀ መዛሙርት ዞር ብሎ "እናንተስ መሄድ ትፈልጋላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው። በዚህ ጊዜ ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ "ጌታ ሆይ! ወደ ማን እንሄዳለን?" ብሎ የመለሰለት።

ይቃል። ያንን ደግሞ ለማድረግ ብዙዎቻችን ፈቃደኞች አይደለንም። ኢየሱስ፣

- *"እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ፥ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ"* ይላል (የማቴ. 16፣24)።

## *6. ለጥቅም ፍለጋ ሲሉ ሌላውን ኮፒ የሚያደርጉ አሉ፥*

በሐዋርያት ዘመን ሲሞን የተባለው ሰው በሰማርያ ከተማ ውስጥ አስማት እያደረገ የሰማርያን ሕዝብ ሲያስደንቅ የቆየ ሰው ነው። ሲሞን አስማት መሥራትን መለማመድ እንዴት እንደ ጀመረ በደንብ አናውቅም። ይሁን እንጂ፤ አስማተኛነቱ በብዙዎች ዘንድ መደነቅን፣ መታወቅን፣ እንዲሁም ብዙ ገንዘብ እንዳስገኘለት ግን እርግጠኞች ነን።

- *"...በከተማይቱ ውስጥ አስማት እያደረገ የሰማርያን ሕዝብ ሲያስደንቅ ቆይቷል፥ እኔ ትልቅ ሰው ነኝ! እያለም ይናገር ነበር። ሰዎች ሁሉ ትንሹም ትልቁም ይህ ሰው ታላቅ ተብሎ የሚጠራው የእግዚአብሔር ኃይል ነው እያሉ ያዳምጡት ነበር። ምክንያቱም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ በአስማት ያስደንቃቸው ስለነበረ ነው"* ይላል (የሐዋ. 8፣9-11)።

አንድ ቀን ወንጌላዊው ፊልጶስ ሲሞን ወደነበረበት፣ ወደ ሰማርያ ከተማ መጥቶ በኃይልና በሥልጣን ሲሰብክ ብዙዎች በክርስቶስ አምነው ተጠመቁ። የእግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ላይ ስለነበረ፣ በአገልግሎቱ ከፍተኛ ውጤት ነበረው። የወንጌል ስበካ ችሎታው፣ እንዲሁም በአገልግሎቱ ውስጥ በግልጽ ይታይ የነበረው ተአምርና ድንቅ ሥራ፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደነበረ ያሳይ ነበር። ፊልጶስ በአጋንንት የተያዙትን ሰዎች በማታለልና በማጭበርበር ሳይሆን በግልጽ አጋንንትን ከሰዎች ሕይወት ውስጥ ገስጾ ያስወጣ ነበር። በልዩ ልዩ በሽታ የተያዙትን፣ አንካሶችና ሽባዎችን በክርስቶስ ስም ይፈውስ ነበር። ሲሞንን ያስደነቀው፣ ፊልጶስ የነበረው ኃይል የሰው ብልሃትና ዘዴ የተጨመረበት፣ ውሸትና





ማጭበርበር የሌለበት መሆኑን በግልጽ ካየና ከተረዳ በኋላ ነው። ፊልጶስ ሥራውን ይሠራ የነበረው፣ በጨለማ ውስጥ፣ ድብቅ በሆነ መንገድ ሳይሆን ግልጽና ፊት ለፊት በሆነ መንገድ ነበር። ኃይሉ ከራሱ የመነጨ፣ ወይም ከክፉ መንፈስ የወጣ ሳይሆን የእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ ሲሞን በደንብ ተረድቷል።

በሲሞን ሕይወት ውስጥ የነበረው ኃይል እርሱ ከነበረው የተለየ በመሆኑ የሚያየው በፍርሃትና በመደነቅ ነበር። ፊልጶስ ወንጌሉን ሲሰብክ የሚያዳምጡትን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በውሃ እንዲጠመቁ ጥሪ ሲያደርግ፣ መንፈስ ቅዱስ ልቡን ስለነካው አስማተኛውም ሲሞንም አምኖ ተጠመቀ።

- *"ሲሞን እንኳን ሳይቀር አምኖ ተጠመቀና ከፊልጶስ ጋር ተባባሪ ሆነ፥ የሚያደርጉትንም ድንቅ ነገሮችና ታላላቅ ተአምራት በማየቱ ይገረም ነበር"* ይላል (የሐዋ. 8፣13)።

በፊልጶስ አገልግሎት ይፈጸም የነበረውን አስደናቂ ሥራ በማየቱ፣ ከፊልጶስ ጋር ተባባሪ ሆኖ በሄደበት ሥፍራ ሁሉ ይከተለው ነበር። ሲሞን አምኖ የተጠመቀው፣ ከልቡ ይሁን ወይም አይሁን አይታወቅም። ሲሞንን ያስደነቀው ውስጣዊው የሆነው ነገር ሳይሆን ከውጪ የሚታየው ነገር እንደሆነ ግልጽ ነው። የሳበውና ያስደነቀው ፊልጶስ የነበረው ኃይል፣ ሰዎች ይሰጡት የነበረውን ክብርና አድናቆት ያይ ስለነበረ ያ ለእርሱ ትልቅ ፈተና ሆኖበት ነበር። *"እኔም ይህን ዓይነቱ ኃይል ቢኖረኝ፤ ብዙዎች ያደንቁኝና ያከብሩኝ ነበር"* በማለት ያስብ እንደነበረ ግልጽ ነው። ሲሞን ክርስቶስን አምኖ የተጠመቀ ቢሆንም፣ የወሰደው የእምነት እርምጃ እውነትነት ያለው ቢሆንም፣ ልቡ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል አልነበረም።

ሲሞንን ያስደነቀው ነገር ያ ብቻ አልነበረም። በአይሁዳውያንና በሰማርያ መካከል የነበረውን ልዩነት ያስታውሳል። በ8ኛው ክፍለ ዘመን አሶርያውያን የሰሜኑን ክፍል፣ እስራኤልን በጦር ድል አድርገው፣ ዋና ከተማቸውን ሰማርያ ላይ አድርገው ነበር። ብዙ እስራኤላውያን ምርኮኞች

ሆነው በአሦራያውያን አገዛዝ ሥር ይኖሩ ነበር። አይሁዶች ከአሦራውያን ጋር ተጋብተው ልጆች ወልደው ይኖሩ ነበር። የደቡቡ ይሁዳ ግን ከ150 ዓመት በኋላ በባቢሎናውያን ጦር ተወግተው ድል ሆነው ቅኝ ግዛት ሲሆኑ፣ ከሌላው ወገን ጋር በመጋባት ንጹሁን የአይሁድ ዘር አንከልስም ብለው የቆዩ፣ በዕዝራና በነህምያ ዘመን ወደ እስራኤል የተመለሱ ነበሩ። እነዚህ አይሁዶች የሰማሪያ ሰዎችን ይጠሏቸውና በጣም ይንቋቸው ነበር። አስማተኛው ሲሞን ይህን በደንብ ያውቃል። ነገር ግን እነዚያ ክርስቶስን አምነው የዳኑ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተለወጡ ክርስቲያኖች፣ ቀድሞ የነበራቸውን ጥላቻቸውንና ልዩነታቸውን አስወግደው ለሳምራውያን፣ ለሚንቋቸው ወንጌልን መስበካቸው ሌላው ያስደነቀው ነገር ነበር።

ወንጌላዊው ፊልጶስ በሰማርያ አገልግሎት ያገኘውን ድል የተመለከቱ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት፣ ሥራው የበለጠ እንዲስፋፋና እንዲጠነክር በማሰብ ከክርስቶስ ጋር በጣም ቅርብ የነበሩትን ዮሐንስንና ጴጥሮስን ላኩላቸው። እነርሱም እጆቻቸውን በበሽተኞች ላይ ሲጭኑ ብዙዎች ከበሽታቸው ሲፈወሱ ሲሞን በማየት በጣም ይደነቅ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ፤ እንዲሁም ከደቀ መዛሙርቱ ወደ ሌሎች አማኞች ሲተላለፍ አየ።

- ***"የሰማርያ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ መንፈስ ቅዱስ ገና በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር። ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጆቻቸውን በጫኑባቸው ጊዜ ሰዎቹ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ"*** ይላል (የሐዋ. 8፤16-17)።

ጴጥሮስና ዮሐንስ እጆቻቸውን በአማኞች ላይ ሲጭኑ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው በምን ይታወቅ ነፀር? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ምናልባት በቋንቋ ተናግረው ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለዚህ የተገለጸ ነገር የለም። እርግጠኛ የምንሆነው መንፈስ ቅዱስን በግልጽ የተቀበሉ መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ሲሞን ራሱ ይህንን በደንብ ያየና የሰማ በመሆኑ ነው። ሲሞን፥





- ***"ሐዋርያት እጆቻቸውን ሲጭኑባቸው መንፈስ ቅዱስ ለሰዎቹ መሰጠቱን ሲሞን ባየ ጊዜ ገንዘብ አመጣላቸውና እኔም እጄን የምጭንበት ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ"*** (የሐዋ. 8፤18-19)።

ሲሞን ይህን ዓይነት ኃይል ቢኖረው የሚያገኘውን ሥልጣን፣ በሰዎች ላይ የሚኖረው ኃይል፣ ሰዎች የሚሰጡት ክብርና አድናቆት እጅግ ከፍተኛ እንደሚሆን አመነ። ስለሆነም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ያላቸውን ኃይል እንዲያካፍሉት ተመኘ። ይህን ዓይነቱ ኃይል በነጻ እንደማይገኝ ስላመነ ይሆናል፣ ምን ያህል ገንዘብ ይዞ እንደመጣ ባናውቅም፣ ገንዘብ አምጥቶ "በእናንተ ውስጥ ያለውን ኃይል ስጡኝ፥ ለዚህም ይህን ያህል ዋጋ እከፍላለሁ" ያለው።

በአስማተኛው ሲሞን ላይ ያየነው ድካም፣ በዘመኑ ባለነው ክርስቲያኖችም ላይ ጎልቶ ይታያል። እንደ ሲሞን የእግዚአብሔርን ኃይል በገንዘብ ገዝተን ለመለማመድ አንሞክር እንጂ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለራሳችን ጥቅም ለማዋል ስንሞክር እንታያለን። ይህን ዓይነቱ ፍላጎት ነው ዛሬ ብዙዎቻችንን ካርቦን-ኮፒ እንድንሆን የሚያደርገን። ወጣት ክርስቲያኖች በነበርንበት ዘመን፤ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በአገራችን በጀመረበት ወቅት፣ የእግዚአብሔር ክብር በግልጽ ይታይ ነበር። በስብሰባዎቻችን ላይ አንዳንዶቻችን ከሌላው እንቅስቃሴ የበለጠ አጋንንት እንዲጮኹ በጣም እንፈልግ ነበር። ለዚህም ትልቁ ምክንያታችን የእግዚአብሔር ኃይል መገለጡ ሳይሆን እጃችንን ስንጭን ሰይጣን እንደሚንቀጠቀጥ ሌሎች ሰዎች አይተው ያለንን ኃይልና መንፈሳዊነት እንዲያደንቁ፣ በዚያም ውስጥ መከበርንና መፈራትን እንድናገኝ ነበር። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን ስንመጣ፣ ይህን ዓይነት ባሕሪ የእግዚአብሔርን ክብር መጋራት ወይም መሻማት እንደሆነ እየገባን ሲመጣ፣ እራሳችንን ማረም ጀመርን። በአሁኑ ዘመን ደግሞ እኛ ከምንሠራው ስህተት በመቶ እጥፍ የባሰ ስህተት ሲሠራ እናያለን።

በመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደ አስማተኛው ሲሞን ብዙ ትርፍ ለማትረፍ የሚፈልጉ ክርስቲያኖች በዘመናችን ብዙዎች ናቸው። *“ለእነ እከሌ ከሠራላቸው፣ እነ እከሌን ከጠቀማቸው፣ ብዙ ስም ካተረፈላቸው፣ ታዋቂ ሆነው በየቦታው እንዲጠሩ በር ከከፈተላቸው፣ እኔ በዚህ ዓይነት ዘዴ የማላገለግልበት ምክንያት የለም። በቅባት እንደማገለግል፣ የጸጋ ስጦታ እንዳለኝ፣ ቪዲዮ አዘጋጆቼ መርጨት አለብኝ”* በማለት፤ ከዚህ ብፊት ሲያገለግሉ ተአምር ተሠራ በተባለበት ሥፍራ የተካሄደውን እንቅስቃሴ በቪድዮ ቀድተው በየቦታው ይረጫሉ። ለመስበክ፣ አለን የሚሉትን ስጦታ በሥራ ላይ ለማዋል ዕድሉ ሲያጋጥማቸው፣ በቪዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን ያዩትንና ያደነቁትን ሰው ለመምሰል፣ እርሱ ያደረገውን ኮፒ አድርገው የሚያደርጉት ግርግር እጅግ በጣም ያሳዝናል። አንዳንዶቹም ሳይፈሩ *“እግዚአብሔር ኢትዮጵያዊው እከሌ ነህ..”* አለኝ፥ በማለት ያንን ሰው ለመሆን ልዩ የሆነ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይታያሉ።

*አስማተኛው ሲሞን ፍላጎቱ የነፍሳት መዳን፣ ወንጌል ያልደረሳቸው እንዲደርሳቸው፣* ብዙዎች የእግዚአብሔርን ክብርና ኃይል አይተው እንዲድኑ በመናፈቅ ሳይሆን፣ ለራሱ የሚያስገኝለትን ክብርና ዝና በማሰብ ነው። አንዳንድ የዘመኑም ክርስቲያኖች፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የሚመኙትና የሚናፍቁት የእግዚአብሔር ክብር እንዲታይ ሳይሆን፣ እነርሱን ታዋቂ እንዲያደርጋቸው ብቻ ነው። እርግጥ ነው እግዚአብሔር በሽተኞችን ይፈውሳል፥ ተአምራትን ይሠራል፥ በመንፈስ ቅዱስ ብዙዎችን ይሞላል። ይሁን እንጂ፣ በዘመናችን ብዙ የምናያቸው ሁኔታዎች አስማተኛው ሲሞን ስጦታውን ለራሱ ጥቅም ለማዋል እንደ ተመኘው፣ እነርሱም ይመኛሉ።

በዘመናችን በወንጌል የሚበለጽጉ ሰዎች እንዳሉ ግልጽ ነው። በአሜሪካ ቴሌቪዥኖች የምናያቸው አንዳንድ የወንጌል ሰባኪዎች ነን የሚሉ እጅግ በጣም የጠገቡ ሀብታሞች ናቸው። በተለይ “የፈውስ፤ የመገለጥ ስጦታ አለን” የሚሉ ሰባኪያን ያላቸውን ብልጽግና የሚያይ ሁሉ፣ ብዙዎች እንደ እነርሱ ለመሆን ከፍተኛ ጉጉት እንደሚኖራቸው የታወቀ ነው። ስለሆነም ያንን ሰው በተቻላቸው መጠን ኮፒ ለማድረግ፣





ልክ እርሱ እንደሚሰብከው ለመስበክ፣ እርሱ እንደሚያደርገው ለማድረግ፣ እርሱ እንደሚጸልየው ለመጸይ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። የሰዎችን አዕምሮ መሳብ የሚችሉበትን ዘዴ ይፈልጋሉ። አስቀድመው ሕዝቡ የሚፈልገው ምን እንደሆን ያጠናሉ። ዛሬ ብዙዎች ስለ ኃጢአት፣ ስለ ቅድስና መስማት አይፈልጉም። ለዚህም ምክንያት አላቸው።

ዘመኑ ክባድ ስለሆነ፤ እንጀራ መብላት የሚችሉት ሰርቀው፣ ዋሽተው፣ አጭበርብረው፣ ቀጥፈው ብቻ የሚመስላቸው አሉ። በዚህ ዓይነት ሕይወት እየኖሩ ክርስቲያን መሆን እንደማይቻል ውስጣቸውም ቢያውቀውም፣ ህሊናቸውን እንዲቆረቁረው የሚያደርገውን ሰባኪ መስማት አይፈልጉም። ሰው በተፈጥሮው ነጻነት የሚሰጠውን “ሃይማኖት” ይፈልጋል። *“ይህን አታድርግ፥ ይህን አትሥራ፥ ይህን አትንካ፥ ይህን አትብላ”* የሚለውን ሃይማኖት አይፈልግም። የሚፈልገው ሙሉ ነጻነት የሚሰጠውን ሃይማኖት ነው። *“በክርስቶስ ብቻ ካመንክ በቂ ነው”* ወይም *“በጸጋው አንዴ ድነሃል፥ ከዚህ በኋላ ይሄ ኃጢአት ነው፥ ያ መተላለፍ ነው መባል የለብህም”* የሚላቸውን ሰባኪ ይመርጣሉ። *“ክርስትና መስቀል የለበትም፥ ጌታን አንዴ ከተቀበልክ ሀብታም ትሆናለህ፥ በሽታ ፈጽሞ አይነካህም”* የሚለውን ሰባኪ ይፈልጋሉ።

ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት በቁጥር መብዛት የሚመስላቸው ሰዎች፣ የአስማተኛው ሲሞንን ዓይነት ፈተና አለባቸው። ለማደግ፣ ለመተለቅ፣ ታዋቂ አገልጋይ ለመሆን ሲሞን የፈለገውን ዓይነት ኃይል መናፈቅ ይጀምራሉ። መናፈቅና መመኘት ብቻ ሳይሆን፣ የሌላው ሰው ካርቦን ኮፒ ለመሆን ጥረት ያደርጋሉ። እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራና እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ እየጠፋ ይመጣል። አድማጮቻቸውን መምረጥ ይጀምራሉ። *“አያምንም፤ አይቀበልም”* ብለው የሚያስቡትን ሰው ከመካከላቸው በተለያየ ምክንያት ገፍተው ማስወጣት ይፈልጋሉ። ቤተ ክርስቲያናቸው ኃብዘው የሚያስብኩትም፣ በሀቅና በእውነት ወንጌልን የሚሰብከውን ሰባኪ ሳይሆን፣ እነርሱን የሚመስለውን፣ የእነርሱን ዓላማ ወደፊት ማስኬድ የሚችለውን፣ ህሊናውን ፈጽሞ የማይቆረቁረውን ሰባኪ ነው። በዚህ መካከል የሚበደለው፣ በመንፈሳዊ ረሀብ የሚያልቀው፣ አዕምሮው

በጥያቄ ተሞልቶ መልስ አጥቶ የሚጨነቀው ምስኪኑ ሰፊው ምዕመን ነው። የሚሰብኩት አልዋጥለት ያለው፣ እውነቱን እውነት ካልሆነው የመለየት ችሎታ ያለው፣ ከቤተ ክርስቲያን ሸሽቶ ይሄዳል። ያም ቢሆን ከቤተ ክርስቲያን በመራቁ፣ *"ጌታ ነቀለልን"* ይሉታል እንጂ፣ *"ዋት ሄደ?"* ብሎ የሚፈልገው አይኖርም።

## 7. መንፈስ ቅዱስን እንደ አስማት የሚጠቀሙ አሉ፥

በዘመናችን ክርስትናን በተዘዋዋሪ እንድ አስማት ሊጠቀሙበት የሚፈልጉ ክርስቲያኖች የበዙበት ዘመን ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸውን በመክፈት ፈንታ፣ መንፈስ ቅዱስ የፈለጉትን ሁሉ የሚያቀርብላቸው ተላላኪያቸው መስሎ የሚሰማቸው አሉ። የመንፈስ ቅዱስን ሙላት፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የሚመኙትና የሚናፍቁት፣ ምድራዊ ጥቅም የሚሰጣቸው እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ክብር የሚያንጸባርቅ፣ ስለ ክርስቶስ የሚመሰክር፣ ክርስቶስን ገልጦ የሚያሳይ መሆኑን ተረድተውት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ የምንፈልገውን ቁሳቁሳዊ ነገር የሚያቀርብልን፣ ባለጸጋ የሚያደርገን የሚመስላቸው አሉ።

አስማተኛው ሲሞን መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት አጥብቆ የተመኘው ስለሚያገኘው የግል ጥቅም በማሰብ እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት፣ በቅድስና ለመኖር የሚያስችለውን ኃይል ፈልጎ አይደለም። ሲሞን ይህን ኃይል ቢቀበል የሚያገኘውን ክብርና ዝና ገምቶ ነው። ይህን ስጦታ ለመቀበል ራሱን መካድ እንዳለበት ግን አልተረዳም ነበር። የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት የሞከረ ሰው ነበር።

- *"...እኔም እጄን የምጭንበት ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ስጡኝ"* በማለት ገንዘብ አምጥቶ ለዮሐንስና ለጴጥሮስ ሰጣቸው።
- *ጴጥሮስ ግን "የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለማግኘት በመፈለግህ ገንዘብህ ካንተ ጋር ይጥፋ! ልብህ በእግዚአብሔር*





*ፊት ቅን ስላልሆነ ከዚህ ነገር ክፍል ወይም ዕጣ የለህም። እንግዲህ በዚህ በክፋትህ ተጸጽተህ ንስሓ ግባ ምናልባት የልብህን አሳብ ይቅር ይልልህ እንደሆነ እግዚአብሔርን ለምን። ምክንያቱም አንተ በመራራ ቅንአት እንደተሞላህና የኃጢአት እስረኛ እንደ ሆንህ አያለሁ"* አለው (የሐዋ. 8፣20-23)።

ጴጥሮስ ሲሞን እንዲያውቅ የፈለገው፣ *"የእግዚአብሔር ስጦታ በገንዘብ እንደማይገዛና እንደማይሸጥ፣ እኛ ለመንፈስ ቅዱስ እንታዘዛለን እንጂ፣ መንፈስ ቅዱስን እኛ ማዘዝ እንደማንችል፣ በእኛ ቁጥጥር ሥር እንደማይውል፣ መንፈስ ቅዱስ የፈቀደውን ያደርጋል እንጂ በሰው ቁጥጥር ውስጥ እንደማይውል"* አልተረዳም ነበር።

መንፈስ ቅዱስን ለግል ጥቅም ማዋል፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለሥልጣን ማትረፊያ ማድረግ፣ እንደ አስማተኛው ሲሞን የተጣመመ ልብ መያዝ ነው። *"በእግዚአብሔር ፊት ቅን ልብ የሌለህ"* ያለው፣ ለዚህ ነው። ሲሞን የክርስቶስ ተከታይ የመሆን ፍላጎት ይኑረው እንጂ፣ ልቡ ግን ፍጹም በኃጢአት የተሞላ ነበር። የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ለማግኘት የፈለገው ለአገልግሎት ሳይሆን፣ ሥልጣንና ክብርን ለማግኘት ነበር። ሲሞን የጴጥሮስን ኃይለኛ ንግግር ሲሰማ፤ በሀዘንና በድንጋጤ ተሞልቶ፣ *"እሁን ከተናገራችሁት አንዳችም እንኳን እንዳይደርስብኝ እናንተ ራሳችሁ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ጸልዩልኝ አላቸው" (የሐዋ. 8፣24)።*

ዛሬ አስማተኛውን ሲሞንን የመሳሰሉ፣ ወንጌሉን የሚሸቃቅጡ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መሆኑን ያልተገነዘቡ፣ ስጦታዎችን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል የሚሞክሩ ብዙዎች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም የበለጠ ከላይ የገለጽናቸውን ዓይነቶች፣ ከመስመር የሚወጡትን በኃይልና በሥልጣን ተሞልተው የሚገስጹ፣ መስመር የሚያስይዙ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ አዲስ ልምምድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያመጡትን *"ልክ አይደላችሁም"* ማለት የሚችሉ፣ በእግባቡ የሚገስጹ እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ አባቶች የሉንም። ችግሩ መንፈሳዊ አባቶች መጥፋታቸው ይሆን? ወይስ አባቶችን የሚያዳምጡ ልጆች

*መጥፋታቸው ይሆን? መልሱ፣ ሁለቱንም ዓይነቶች የሉም። መገሰጽ የሚያስችል አቅምና ዕውቀት ያላቸው የሉም ማለት ሳይሆን፣ ብዙዎች "ተቀባይ ያሳጣኛል" ብለው በመፍራት እጆቻቸውን አጣምረው፣ አፋቸውን ዘግተው የተቀመጡ በመሆናቸው ነው።*

የወንጌል መሠረታዊ የሆነ ዓላማ ምንድነው? እርግጥ ነው ትርፍ እንጂ፣ ኪሳራ የለበትም። ትርፋም ጊዜያዊ፣ ወይም ምድራዊ ነገር ሳይሆን ዘላለማዊ ነው። እግዚአብሔር የጠራን የግል ጥቅሞቻችንን እንድናካሂድ አይደለም። የጠራን መስቀሉን እንድንሸከም፣ ራሳችንን መስዋዕት አድርገን እንድንሰጥና ራሳችንን ዝቅ አድርገን እንድናገለግል ነው። ራሳችንን ለአገልግሎቱ እንድንሰጥ፣ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ ኃይልና ሥልጣን እንዲኖረው ይጠራናል።

የሲሞን ችግር በእርግጥ ብዙዎቻችን ካለን ችግር የተለየ አልነበረም። ወደ ክርስቶስ ለመምጣት መፈለጋችን የግል ጥቅም ይገኝ በታል ብለን፣ ወይም ራሳችንን ለመጥቀም ብለን ይሆን? ጥቅም የምናገኝበት መስሎ ከታየን፣ ክርስቶስን ለመከተል ፈቃደኞች እንሆን ይሆናል። ለአንዳንዶቻችን ወንጌል የተሰበከልን፣ *"ወደ ጌታ ብትመጡ ችግራችሁ ሁሉ ይቃለላል፥ ባለጸጋ ትሆናላችሁ፥ ፈተናና ችግር አያጋጥማችሁም"* ተብለን አይደለም። እግዚአብሔር እኛን በማባበል፣ "ትርፍ አለበት" ብሎ አይጠራንም። የሚጠራን *"ና! ና! ሙትልኝ!"* ብሎ ነው። ጴጥሮስ ለሲሞን የሰጠው ምክር፤

- *"... በዚህ በክፋትህ ተጸጽተህ ንስሀ ግባ ምናልባት የልብህን አሳብ ይቅር ይልልህ እንደሆን እግዚአብሔርን ለምን። ምክንያቱም አንተ በመራራ ቅንአት እንደተሞላህና የኃጢአት እስረኛ እንደ ሆንህ አያለሁ" አለው (የሐዋ. 8፣22-23)።*

የምናደርገውን ነገር በእርግጥ አምነንበት ነው ወይስ ሌሎች ስላደረጉት ብቻ ነው የምናደርገው? የራሳችን አቋም የሌለን፣ ከሚፈሰው ጋር የምንፈስ ነን? የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የምንመኘውና የምንፈልገው፣ ጥቅም እንዲያስገኝልን ነው ወይስ የእግዚአብሔር ክብር በእኛ





ሕይወት እንዲታይ ነው? ኢየሱስን እንምሰል እንጂ፣ የምናደንቀውን ሰባኪ ለመሆን ወይም ለመምሰል አንሞክር። እግዚአብሔር ማንንም ሳንመስል፤ ልክ እንዳለነው ይወደናል። የክርስትና ሕይወት ካርቦን ኮፒ አይደለም። ራሳችንን ሆነን እንድንኖር፣ እንድናገለግለው፣ የራሳችን የሆነ ልምምድ እንዲኖረን እግዚአብሔር ይፈልጋል። እግዚአብሔር ሲፈጥረን ደስ ብሎት እንደሆን አንጠራጠርም። እግዚአብሔር የፈጠረን እንደ ድንገት ሳይሆን፣ በእኛ ሕይወት ፈቃዱን ለመፈጸም ነው።

ይህ እውነት ከሆነ ለምንድነው ብዙዎች ራሳቸውን እንዳሉ መቀበል የሚያቅታቸው? ለምንድነው ራሳቸውን ወይም ማንነታቸውን ለመለወጥ የሚሞክሩት? የሚያስደንቀው አንዳንድ ሰው ራሱን ይውደድ እንጂ፣ ራሱን መሆን የማይፈልግበት ምክንያቱ አይገባንም። የእኛ ትልቁ ጠላታችን ሌላ ሰው ሳይሆን፣ እኛው ራሳችን ነን። ከውስጣችን የሚጮኽ ድምጽ አለ። "እከሌን ምሰል፤ እርሱ የሚሠራውን ሥራ፣ ሕዝቡ የሚያደርገውን ተከትለህ አድርግ" የሚል ንዝንዝ፣ ብዙ ግፊት በየአቅጣጫው ይደርስብናል።

*ምን ማድረግ፣*

*ምን መልበስ፣*

*ምን መግዛት፣*

*ምን መሆን፣*

*በጠቅላላው ምን ዓይነት ሕይወት መኖር እንዳለብን*
*የሚነግሩንን ብዙ ድምጾችን እንሰማለን።*

*በሃሳባቸው እንድንስማማ፣*

*የእነርሱን ቅርጽ እንድንይዝ፣*

*በሄዱበት መንገድ እንድንሄድ፣*

*የእነርሱን እርምጃ ተከትለን እንድንሄድ*

*በየአቅጣጫው ብዙ ጥያቄዎች፣ ብርቱ ግፊት ይደርስብናል።*

ከምንሰማው የተለያየ ድምጽ የተነሳ ማንነታችንን በትክክል ለማወቅ ግራ የምንጋባበት ጊዜ አለ። ቆም ብለን እስካሁን አልፈን የመጣን በትን እያየን፣ ከዚህ በኋላ የት መድረስ እንዳለብን የራሳችንን ምርጫ መምረጥ አለብን። የዛሬ 10፣ 20፣ 30 ዓመት እንደነበርነው አይደለንም። ማርጀታችንን፣ መልካችን መለወጡን ማለቴ አይደለም። በእኛነታችንም ብዙ ተለውጠናል። በሕይወታችን ብዙ ዓይነት ምርጫዎችን መርጠን፣ ብዙ ውሳኔዎችን ወስነናል። እነዚህ ምርጫዎቻችንና ውሳኔዎቻችን ብዙ ለውጠውናል። ምርጫዎቻችንና ውሳኔዎቻችን ምን እንደምንሆንና ወዴት እንደምንሄድ ያሳዩናል።

*የሌሎች ሰዎች ፎቶ ኮፒ ነን? ወይስ የሆንነውን ነን?*

*ወደነፈሰበት የምንነፍስ፣ ወደ ገፉን አቅጣጫ የምንገፋ ነን?*

*ወይስ የራሳችን አቋም ያለን ነን? ጌታ እንድንሆን የሚፈልገውን ለመሆን እንጥራለን?*

*ወይስ ሌሎች እንድንሆን የሚፈልጉትን ዓይነት ሰው ለመሆን እንጥራለን። አሁንም ምርጫው የራሳችን ነው።*

እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን ዓይነት ሰው ለመሆን፣ ዓይናችንን ከሰዎች ላይ አንስተን በእግዚአብሔር ላይ ማሳረፍ አለብን። ሰዎች አቅጣጫችንን ያስለውጡናል። እግዚአብሔር ግን መንገዳችንን ስተን እንዳንሄድ ይጠብቀናል። በአገልግሎት ውስጥ ራሳችንን በመሆን ፈንታ ሌላውን ሰው ለመምሰል ወይም ለመሆን የምንሞክርበት ጊዜ አለ። ያም ይጎዳናል እንጂ አይጠቅመንም። በቤተ ክርስቲያን ትልቁ ችግር ብዙ ክርስቲያኖች ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌሎችን ለመኮረጅ (ለመሆን) ጥረት ስለሚያደርጉ ነው። በአገልግሎት ውስጥ ሌሎችን ኮርጀው ለማገልገል ሲሞክሩ ያስታውቅባቸዋል። ያለአግባብ ይጮኻሉ፤ ያለ አግባብ ይወራጫሉ። መድረኩ አይበቃቸውም። የሚያዩዋቸው ሰዎች "ይቺኛው ከእከሌ የተኮረጀች ናት" ማለት ይችላሉ።





## *8. ራሳችንን እንመርምር።*

ራሱን የማይመረምር፣ ራሱን የማይጠይቅ ለራሱ እውነተኛ ዕድገትን ይነፍጋል። "መንፈስ ጠንካራነት የሚታይብኝ ነኝ? ክብሬንና ስሜን የምጠብቅ ነኝ?" በማለት ሁልጊዜ ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል።

*"ለዝና ስል፣ ኑሮዬን ለማመቻቸት ስል፣ ከእኔ የማይጠበቀውን ዓይነት ባሕሪ የማሳይ ነኝ?*

*ለጊዜያው ጥቅም ስል ስለ ገጸ ባሕሪዬ (character) ግድ የሌለኝ ነኝ?" ብለን ራሳችንን መመርመርና መጠየቅ ይገባናል።*

*ችግር ውስጥ ቢከተኝም፣ የሚሰማኝን ሳልደብቅ እውነቱን የምናገር ሰው ነኝ?*

*የአቋም ሰው ነኝ? በያዝኩት አቋም የማላወላውል፣ ዛሬ አንድ ነገር፣ ነገ ሌላ ነገር የምልና የምሆን፣ የምለዋወጥ ነኝ?*

*ከአንድ እውነተኛ አማኝ የሚፈለግበትና የሚጠበቅበትን ባሕሪ የማንጸባርቅ ነኝ?*

*ለልቤ ከማይሞሉልኝ ሰዎች ጋር ከመሰለፍ ይልቅ፣ ብቻዬን ለመቆም ቆራጥነት ያለኝ ነኝ?*

*ዛሬ እውነተኛ ሰው በጠፋበት፣ "የሰው ያለህ" በሚባል በት ዘመን ካሉት ጥቂት መልካም የሆነ ገጸ ባሕሪ ካላቸው ሰዎች መካከል እቆጠር ይሆን?*

መልካም ገጸ ባሕሪ (character) ያላቸው ሰዎች፣ ጽኑ አቋም (integrity) ያላቸው ናቸው። የሚናገሩትም ሆነ የሚያደርጉት ለእግዚአ ብሔር ሙሉ በሙሉ ከተሰጠ ሰው ልብ የሚወጣው ነው። መልካም ገጸ ባሕሪ፣ ማለት ውስጣዊ ሙሉነት ማለት ነው። ጽኑ አቋም ያለን ሰዎች ከሆንን ግብዞች ሆነን ሌሎችን አናታልልም፤ ያልሆንነውን "ነን" ብለን ራሳችንንና ሌሎችን አንዋሽም። ሐዋርያው ጳውሎስ፣

ለሕይወቱ ልዩ የሆነ ዓላማ እንዳለው በመረዳት እንዲህ ዓይነቱን ሀሳብ ማስተናገዱን አቆመ።

ኒክ እግዚአብሔር እጅና እግር እንዲሰጠው ጸለየ። እግዚአብሔር ጸሎቱን የማይመልስለት ከሆነ፣ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ እርሱን እንደማይመሰግነው ነገረው። ይሁን እንጂ፣ አንድ ቀን እናቱ ፍጹም አካለ ስንኩል ስለሆነ አንድ አሳዛኝ ታሪክ የያዘ የዕለት ጋዜጣ ሰጠችውና ካነበበ በኋላ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚያልፍ እርሱ ብቻ እንዳልሆነ ሲገነዘብ፣ እጅና እግር የሌለው ሆኖ መፈጠሩን በጸጋ ተቀበለው። ከዚህ በኋላ አካለ ስንኩል ሆኖ በሕይወቱ ስኬትን ካገኘ ለብዙ ሰዎች መነቃቂያ መሆኑን ስለተገነዘበ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመረ።

ኒክ እጅና ጣት፣ እግርና የእግር ጣቶች ሳይኖሩት በየቀኑ፣ ቀስ በቀስ ሙሉ ሕይወት መኖር የሚያስችለውን ዘዴ መማር ጀመረ። በትንሹ ግራ እግሩ ላይ ሁለት የእግር ጣቶች ስላሉት እነርሱን በመጠቀም መጻፍ ጀመረ። ተረከዙንና አንድ የእግር ጣት በመጠቀም 45 ቃላት በደቂቃ ታይፕ ማድረግ ቻለ። የቴኒስ ኳስ መወርወር፣ ታምቡር መጫወት፣ በብርጭቆ ውሃ ቀድቶ መጠጣት፣ ጸጉሩን ማበጠር፣ ጺሙን መላጨት፣ ጥርሱን መቦረሽ፣ የስልክ ጥሪ መቀበልና መደወል፣ ጎልፍ መጫወት፣ ዋና መዋኘትና እንዲሁም የፓራሹት ዝላይ መለማመድ ቻለ።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት፣ ኒክ የተማሪዎች መማክርት (student counsel) አባል በመሆን ለአንዳንድ በጎ አድራጎት ማህበራት እንዲሁም አካለ ስንኩል የሆኑትን ለሚረዳ የበጎ አድርጎት ማህበራት ዕርዳታ በማሰባሰብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርግ ነበር። የ17 ዓመት ወጣት ሆኖ የአንድ የጸሎት ጓድ አባል ሆኖ አንዳንድ ንግግሮችን ያቀርብ ነበር። በመጨረሻ “ሕይወት ያለ እጅና እግር” (Life Without Limbs) የሚል ድርጅት መሠረተ። የሚያስደንቀው ነገር ኒክ





በተአምር ስለሚያምን አንድ ቀን እግር ይኖረኛል በማለት ጫማ ቁም ሣጥኑ ውስጥ ያስቀምጥ እንደነበረ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ጠቅሶታል።

በአሁኑ ጊዜ ኒክ ካሊፎርኒያ እስቴት፣ ሎስ አንጀለስ ከተማ ውስጥ ይኖራል። የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ካኔ ሚያሃራ የተባለችውን ወጣት አግብቶ ትዳር መስርቶ ይኖራል። ባልሰለጠነው በሦስተኛው ዓለም ውስጥ ቢኖር ኖሮ እንዲህ ዓይነት ጤናማ ያልሆነ አካል ይዞ የሚወለድ ህጻኑ የተረገመ ነው ተብሎ ስለሚታመን ልክ እንደተወለደ በወላጆቹ እጅ ይገደል ነበር።

ኒክ በ21 ዓመቱ ከሪፈትዝ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግና በፋይናንሻል ፕላኒግ የመጀመሪያ ዲግሪውን አገኘ። ወጣቶችን በሚመለከት ነጥብ ላይ በዓለም ዙሪያ እየተዘዋወረ የማበረታቻ ንግግር አድራጊ ሆነ። በአጭር ጊዜ ውስጥ በሃያ አራት አገሮች፣ በ5 አህጉራት እየተዘዋወረ ከ3 ሚሊዮን ለሚበልጥ ሕዝብ የማበረታቻ ንግግር አድርጓል። ኒክ ዌብ ሳይቱ ላይ ስለ ራሱ ሲጽፍ እንዲህ ይላል።

“ኒክ እባላለሁ። ከ30 ዓመት በፊት እጅና እግር የሌለኝ ሆኜ በመወለዴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። አካለ ስንኩል ሆኜ በመፈጠሬ ኑሮዬ ቀላል ነው” ብዬ አልዋሻችሁም። ይሁን እንጂ፣ በሚወዱኝ ወላጆቼና ወዳጆቼ እርዳታ፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ ባለኝ እምነት በሕይወቴ ውስጥ ያጋጠሙኝን ዕንቅፋቶችን ሁሉ ለመወጣት ጉልበት አገኘሁ። በአሁኑ ወቅት ከባለቤቴ ከካኒ ጋር ካሊፎርኒያ ውስጥ ዓላማ ያለውና በደስታ የተሞላ ሕይወት እየኖርኩ ነው። በብዙዎች ሰዎች ሕይወት መልካም የሆነ ተጽዕኖ በማድረጋችንና የብዙዎች ሕይወትም ሲለወጥ በማየታችን እኔም ሆንኩ ባለቤቴ በጣም ደስተኞች ነን።

ክፉ ነገር፣ ለሌለንና ላጣነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ምክንያት አናደርገውም ነበር። *"እግዚአብሔር ክፉ ስለሆነ ክፉ ነገር አደረገብኝ፤ ሥጋዬን በበሽታ መታ"* የሚል እምነት ወደ ውስጣችን ዘልቆ እንዲገባ መፍቀድ የለብንም። ዕንባቆም እግዚአብሔር ፍጹም፣ ንጹህና ቅዱስ መሆኑን ሲናገር፡ *"ዐይኖችህ እጅግ ንጹሓን ስለሆኑ ክፉ ነገርን አይመለከቱም፤ ክፉ ነገር ሲሠራ አይተህ መታገሥ አይሆንልህም...."* ይላል (ዕን. 1፥13)።



3

# *ካርቦን-ኮፒ ከመሆን፣ ራስን መሆን ይቀላል*

- *"እግዚአብሔር አይለወጥም፤ እርሱንም የሚቃወም የለም፤ እርሱ የወደደውን ሁሉ ያደርጋል። ለእኔ ያቀደውን ሁሉ ይፈጽመዋል ..."*

  *(ኢዮብ 23፥13-14)።*

- *"በዓለም ላይ ቀላሉ ነገር ራሳችንን መሆን ነው፤ ከባዱና አስቸጋሪው ነገር፣ ሌሎች እንድንሆን የሚፈልጉትን መሆን ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዲያስቀምጡን አንፍቀድላቸው" –ሊዮ ቡስካግሊያ*

- *"የራሱ የሆነ ግላዊ አመለካከት የሌለው፣ ወይም በሌሎች ሰዎች አመለካከት የሚደገፍ፣ ነጻነት የሌለው ባሪያ ነው። ሌላውን ሰው ለመሆን መመኘት (ማለም)፣ በራሳችን ሳንጠቀም መቅረት ነው" –ፍሬዴሪክ ክሎፕስቶክ*

እርካታ ያጡ፣ ደስታ የሌላቸው፣ ተስፋ የቆረጡ ራሳቸውን በመሆን ፈንታ ሌላውን ለመሆን የሚሞክሩ፣ ማድረግ የሌለባቸውን ለማድረግ የሚታገሉ ብዙ ናቸው። የኮንጎሊስ ምሳሌ *"እንጨት አስር ዓመት ውሃ ውስጥ ቢቆይ አዞ አይሆንም"* ይላል።[6] እግዚአብሔር እንጂ፣ እኛ ራሳችንን መለወጥ አንችልም። *ካርል ሮጀርስ* የተባለው ጸሀፊ "እውነትን

[6] John Mason, Imitation is Limitation, Bethany House, Minneapolis, MN, 2004.